ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ረቡዕ
82ኛ ዓመት ቁጥር 186 መጋቢት 6 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# ለ2015/16 ምርት ዘመን ለአፈር ማዳበሪያ ግዥ 21 ቢሊዮን ብር ድጎማ ተደርጓል

## - አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ወደ ክልሎች ተጓጉዟል


ፎቶ - በሐዲስ አብርሃ

ዶክተር ግርማ አመንቴ

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- ለ2015/16 የመኸር ምርት ዘመን መንግሥት ለአፈር ማዳበሪያ ግዥ 21 ቢሊዮን ብር ድጎማ ማድረጉን የግብርና ሚኒስቴር ገለጸ፡፡ ለምርት ዘመኑ 12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል የማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሞ አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ወደ ክልሎች መጓጓዙ ተጠቁሟል፡፡

የግብርና ሚኒስትሩ ዶክተር ግርማ አመንቴ የግብዓት አቅርቦትን አስመልክተው ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ መንግሥት በ2015/16 ምርት ዘመን ጥቅም ላይ በሚውለው የማዳበሪያ ዋጋ ላይ 21 ቢሊዮን ብር ድጎማ እንዲደረግ ወስኗል፡፡ ይህ ድጎማም በአማካይ በአንድ ኩንታል ማዳበሪያ ዋጋ ላይ አንድ ሺህ 566 ብር ቅናሽ አለው፡፡ ከትናንት ወዲያ ጀምሮ ክልሎችም የዘንድሮውን የማዳበሪያን ዋጋ እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡

የግብርናን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ መንግሥት በማዳበሪያ ዋጋ ላይ ድጎማ እንዲደረግ መወሰኑን አመልክተው፤ የማዳበሪያ ዋጋው አሁን ካለው የትራንስፖርትና የዓለም የማዳበሪያ ዋጋ ጭማሪ አንጻር ተመጣጣኝ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ይህም በየዓመቱ እየተመዘገበ ያለው የግብርና ምርታማነት በማዳበሪያ አቅርቦት ምክንያት እንዳይስተጓጎል ለማድረግና የአርሶ አደሩን ጫና ለማገዝ ታስቦ መሆኑን ነው የተናገሩት፡፡

መንግሥት በ2014/15 ምርት ዘመን የማዳበሪያ ዋጋ ላይ 15 ቢሊዮን ብር ድጎማ ማድረጉን አስታውሰው፤ ይህም በአማካይ በአንድ ኩንታል ማዳበሪያ ላይ አንድ ሺህ 100 ብር ቅናሽ ተደርጓል፡፡ ዘንድሮም አምና ከነበረው የማዳበሪያ ዋጋ ጭማሪ ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን መደረጉን ሚኒስትሩ አብራርተዋል፡፡

ዘንድሮ ለ2015/16 ምርት ዘመኑ ተብሎ ከተገዛው 12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ አራት ነጥብ 05 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ወደ ክልሎች ተጓጉዟል ያሉት ዶክተር ግርማ፤ ከዚህ ውስጥም ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መጋዘን መድረሱን ጠቁመዋል፡፡

ባለፈው ዓመት ተገዝቶ ጥቅም ላይ ሳይውል ተከማችቶ ከሚገኘውን ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ጨምሮ 15 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለ2015/16 ምርት ዘመን ለበጋ መስኖ፣ ለበልግና ለመኸር ጥቅም ላይ የሚውል መሆኑን ገልጸው፤ ጥቅም ላይ ሳይውል

ለ2015/16 ምርት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል












ፎቶ - በሐዲስ አብርሃ

## ከኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ከ48 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

ገጽ 4

# የመዲናዋን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ለመፍታት በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት 6 ወራት የአዲስ አበባ ከተማ የነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታት በርካታ ውጤታማ ሥራዎች መከናወናቸውን ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ለሁለት ቀናት የሚቆይ 2ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 3ኛ መደበኛ ጉባዔውን ከትናንት ጀምሮ በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ የ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6 ወራት የሥራ አፈጻጸም ለምክር ቤቱ ባቀረቡበት ወቅት እንደተናገሩት፣ ባለፉት 6 ወራት የመዲናዋን ፖለቲካዊ፤ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መዋቅራዊ ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ለመፍታት ባለድርሻ

የመዲናዋን ኢኮኖሚያዊና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ - ገባቦ ገብሬ








# የሰንበት ቀን ገበያዎች ተደራሽነታቸው ሲሰፋ እንደሚገባ ነዋሪዎች ተናገሩ

## - አስተዳደሩ ገበያዎቹን ለማስፋፋት በትኩረት እንደሚሠራ አስታውቋል

**ታደሰ ብናስፈው**

አዲስ አበባ፡- የሰንበት ቀን ገበያዎች የሸማቹን አቅም ያገናዘቡ በመሆናቸው ተደራሽነታቸው ሊሰፋ እና የግብይት ሥርዓታቸው ሊጠናከር ይገባል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ተናገሩ። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በበኩሉ የሰንበት ቀን ገበያዎች ተደራሽነታቸው እንዲሰፋ እና የተሳለጡ እንዲሆኑ እንደሚሠራ አስታውቋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክፍለ ከተማ የስድስት ኪሎ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ሃና ዮሐንስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሰንበት ቀን ገበያ ማኅበረሰቡ የሚፈልገውን ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኝበት የገበያ ቦታ ሆኗል። በስድስት ኪሎ የሰንበት ቀን ገበያ ለግብይት የሚቀርቡ ምርቶች ነጋዴዎች በመደበኛ የመሸጫ ማዕከላት ከሚሸጡበት ዋጋ በተመጣጣኝ ዋጋ ለገዥዎች ያቀርባሉ። በመሆኑም አሁን ያለውን ተደራሽነት ከዚህም በላይ ማስፋፋት ቢቻል የሚል ሀሳብ አቅርበዋል።

በየካ ክፍለ ከተማ የመገናኛ ነዋሪ የሆነችው ወይዘሪት ፍሬህይወት ጫንያለው በበኩሏ፤ የሰንበት ቀን ገበያ ሸቀጣቀጦችን፣ አትክልቶችንና የቤት አስቤዛዎችን ከሱቆች ዝቅባለ የግብይት ዋጋ እያቀረቡ ነው። የገበያ ተደራሽነቱን በማስፋፋት የተለያዩ የጥራጥሬ፣ የጤፍ፣ የበቆሎ፣ የገብስና የመሳሰሉ ምርቶችንም በገበያው በይበልጥ ለአቅርቦት የሚውሉበት መንገድ ቢፈጠር የኑሮ ውድነቱን ለማርገብ ያግዛል ብላለች።

በአራዳ ክፍለ ከተማ የፒያሳ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ እሸቴ አሰፋም የሌሎችን ሃሳብ ይጋራሉ። የሰንበት ቀን ገበያ በመዲናዋ መኖሩ ሸማቹ ኅብረተሰብ የሚፈልገውን የሸቀጣሸቀጥ ዕቃዎችን፣ ፍራፍሬዎችንና አትክልቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት እንዲችሉ አድርጎታል። ከአንድ ኪሎ አትክልትና የቤት አስቤዛ ቢያንስ የአምስት ብር ቅናሽ እንደሚገኝበት ገልጸው፤ የሰንበት የገበያ ቀን የተለያዩ ሸቀጣቀጦች፣ አትክልቶችንና የቤት አስቤዛዎች በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት የሚቻልበት የገበያ ማዕከል ነው በመሆኑም



ምክትል ከንቲባ አቶ ዣንጥራር ዓባይ

ሊስፋፋ እና የገበያ ሥርዓቱ ሊዘምን ይገባል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ጥላሁን ጌታቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት በአምስት ክፍለ ከተሞችና በአምስት የሰንበት ቀን የገበያ ቦታዎች የተጀመረው የሰንበት ቀን ገበያ አሁን ላይ በ11 ክፍለ ከተሞች በማስፋፋት በ137 የገበያ መዳረሻዎች እየተሠራ ነው።

ከክልል ከሚገኙ የገበሬ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋር የተሳለጠ የግብይት ሥርዓት በመዘርጋት ማኅበረሰቡ የግብርና ምርቶችን በቅርበትና በቀላሉ እንዲያገኝ በስፋት እየተሠራ ነው ብለዋል።

በሰንበት ገበያ ሸማች ማህበሩ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ብር ብድር ከከተማ አስተዳደሩ ተመቻችቶለት ቀይ፣ ነጭ እና ሰርገኛ ጤፍ እንዲሁም በቆሎ እና የመሳሰሉ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ እያደረገ መሆኑን



አስረድተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ አቶ ዣንጥራር ዓባይ በሰጡት ምላሽ በከተማ አስተዳደሩ የተጀመሩ የሰንበት ቀን ገበያዎች እንዲስፋፉ እና የአቅርቦት ሰንሰለታቸው የተሳለጠ እንዲሆን እየተሠራ ነው ብለዋል።

119 የነበረውን የሰንበት ቀን ገበያን ወደ 126 በማሳደግ ማኅበረሰቡ ምርቶችን በቅናሽ ዋጋ የሚገዛበት ዕድል ተፈጥሯል ያሉት ምክትል ከንቲባው፤ በገበያውም ሸማቹ ማኅበረሰብ የተለያዩ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ መገበያየት ችሏል ነው ያሉት።

አምራቾች ምርታቸውን በቀጥታ ወደ ገበያው እንዲያቀርቡ መደረጉ በሸማች እና በሻጮች መካከል ያለውን ደላላ ከማስቀረቱም ባለፈ የሚቀርቡ የምርቶች ዋጋቸው ገበያ ላይ ካለው ቅናሽ ነው። የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት የአትክልት ምርቶች ከሚገኙበት አካባቢ ጋር የገበያ ትስስር ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ ነው ሲሉ አብራርተዋል። አምራቾች ምርታቸውን በቀጥታ ለገበያ እንዲያቀርቡ የማድረግና የሰንበት ገበያውን አጠናክሮ ለማስቀጠል በከተማ አስተዳደሩ በኩል እየተሠራ መሆኑን አቶ ዣንጥራር አመላክተዋል።

# በበልግ ዝናብ የጎርፍ አደጋ እንዳይደርስ አስፈላጊው ቅድመ ጥንቃቄ ሲደረግ ይገባል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣዮቹ አሥር ቀናት የሚጥለው የበልግ ዝናብ የጎርፍ ተጠቂ በሆኑ የተፋሰስ አካባቢዎች ላይ አደጋ እንዳያስከትል አስፈላጊው ቅድመ ጥንቃቄ ከወዲሁ ሊደረግ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

ኢንስቲትዩቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚስተዋለው የዝናብ ሁኔታ አብዛኛውን የበልግ ርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰስ የሆኑ አካባቢዎችን የሚሸፍን ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተስፋፋና የተጠናከረ ርጥበት ያገኛሉ። በዚህም ዝናቡ የጎርፍ ተጠቂ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ጉዳት እንዳያስከትል አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቄ ከወዲሁ ሊደረግ እንደሚገባ ተመላክቷል።

ኢንስቲትዩቱ የላከው መግለጫ እንደሚያትተው፤ አብዛኛው አሞ ጊቤ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ ገናሌ ዳዋ፣ የላይኛውና መካከለኛው ዋቢ ሸበሌ፣ የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ ተከዜና ዓባይ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት የሚያገኙ ናቸው። ይህም ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን የገጸ ምድር የውሃ መጠንን ሊያሻሽል እንደሚችል ይጠበቃል።

በአጠቃላይ በመጪዎቹ አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ እና ምዕራብ ሸዋ ዞኖች እንዲሁም አርሲና ባሌ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ ጉጂ አካባቢዎች በአብዛኛው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ ብሏል መግለጫው።

በተመሳሳይ ቦረናና ሞያሌ፣ ከጋምቤላ ክልል የማጃንግ ዞን፣ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ የአሶሳና የካማሺ ዞኖች፣ ከትግራይ የደቡብ እና የምሥራቅ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ዋግ ኽምራ፣ ባህር ዳር፣ እንዲሁም ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም ዞኖች በአብዛኛው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ተብራርቷል።

በተጨማሪም ጥቂት የደቡብና የሰሜን ጎንደር ቦታዎች አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የሲዳማ ክልል፣ የአፋር ክልል ዞኖች እና የሶማሌ ክልል ዞኖች በአብዛኛው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው በመግለጫው ተጠቁሟል።

በጥቂት ቦታዎች ላይ ደግሞ በተለይም ደቡብ አፋር፣ ምሥራቅ ሸዋ እና የደቡብ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የተላከው የትንበያ መረጃ ያሳያል።

# ከ20 ወራት መቋረጥ በኋላ የሀራ ከተማ ነዋሪዎች የኤሌክትሪክ አገልግሎት አገኙ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት በሀራ ከተማ ለ20 ወራት ተቋርጦ የቆየው የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጠት መጀመሩን በሰሜን ወሎ ዞን የሀራ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

የሀራ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ መሀመድ ሰኢድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በከተማው ለአንድ ዓመት ከስምንት ወር ተቋርጦ የቆየው የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጠት የጀመረ ሲሆን፤ ይህም ለከተማዋ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

የኤሌክትሪክ አገልግሎት በመቋረጡ የከተማዋ ነዋሪዎች ከፍተኛ ለሆነ የውሃ ችግር ተዳርገው የነበሩ ቢሆንም፤ አሁን ላይ የውሃ እና የኤሌክትሪክ አገልግሎት ችግር ሙሉ በሙሉ መቀረፍ ችሏል ብለዋል።

በሀራ ከተማ 10 ትራንስፎርመሮች በጦርነቱ ምክንያት በደረሰባቸው ጉዳት አገልግሎት ማግኘት እንዳይቻል አድርጎ መቆየቱን አንስተው፤ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ስድስት ትራንስፎርመሮችን ለከተማዋ ድጋፍ በማድረጉ ከተማዋ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን መቻሏን አብራርተዋል።

የኤሌክትሪክ አገልግሎት መጀመሩ ከተማዋ በኢኮኖሚ እንድታድግ፣ ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ እና ከሥራ ውጪ ሆነው የነበሩ ነጋዴዎችና ወጣቶች ወደ ሥራቸው መመለስ እንዲችሉ ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል። እንደ አቶ መሀመድ ገለጻ፣ ችግሩ መቀረፍ የቻለው ከፌዴራል እስከ ዞን ባሉ የመንግሥት አካላት ርብርብ ሲሆን፤ ለተደረገው እገዛ አመስግነዋል።

የወልዲያ ከተማ ዲስትሪክት ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ ወልደሰማያት በበኩላቸው፤ በአካባቢው ተቋርጦ የነበረው የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጠት እንዲጀምር ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጀምሮ በትኩረት ሲሠራ እንደነበር ገልጸው፣ አሁን ላይ በከተማዋ አገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ ጀምሯል ብለዋል። ስድስት ትራንስፎርመሮችን ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በመገኘቱ ችግሩ ሙሉ በሙሉ ተፈትቷል ብለዋል።

ከጦርነቱ በተጨማሪ የሀራ ከተማ ትራንስፎርመሮች ውስጥ ያለው ዘይት በመዘረፉ ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ መሆናቸውን ያስታወሱት ዳይሬክተሩ፤ ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር ሁሉም ማኅበረሰብ የአካባቢውን መሠረተ ልማት በንቃት ሊጠብቅ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የሀራ ከተማ ነዋሪና የብረታ ብረት ሠራተኛ አቶ ሁሴን ሰይድ የኤሌክትሪክ አገልግሎት በመቋረጡ ለረጅም ጊዜ ከሥራ ውጪ በመሆኔ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ እና የሥነ ልቦና ጉዳት ደርሶብኝ ነበር ብለዋል። አሁን ላይ አገልግሎቱ በመጀመሩ ወደ ሥራቸው መመለስ የሚችሉ በመሆናቸው መደሰታቸውን ገልጸዋል።

ሌላኛው የሀራ ከተማ ነዋሪ አቶ ሰይድ አሊ በበኩላቸው፤ በከተማዋ ለአንድ ዓመት ከስምንት ወር ተቋርጦ የነበረው የኤሌክትሪክ አገልግሎት በመጀመሩ መደሰታቸውን ተናግረዋል። የከተማዋ ነዋሪዎች የኤሌክትሪክ አገልግሎት በመቋረጡ ምክንያት ከደረሰባቸው የኢኮኖሚ እና ሥነ ልቦና ጉዳት እንዲወጡ ያደርጋልም ብለዋል።

በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የምትታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ በየካቲት 25 2015 ዓ.ም ዕትሟ የሀራ ከተማ ነዋሪዎች የኤሌክትሪክና የውሃ አገልግሎት በመቋረጡ ምክንያት መቸገራቸውን እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በቅርቡ አገልግሎቱን እንደሚያስጀምር መዘገቡ የሚታወስ ነው።



አቶ ንጉሡ ጥላሁን

## ባለፉት ስምንት ወራት ከሁለት ሚሊዮን 84ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

### - የሥራ ፈጣሪነት አስተሳሰብ አለመዳበር ለሥራ ዕድል ፈጠራው ተግዳሮት ሆኗል

**አዲሱ ገረመው**

ደብረብርሃን፡- ባለፉት ስምንት ወራት ከሁለት ሚሊዮን 84ሺ በላይ ዜጎች የሥራ ዕድል እንደተፈጠረላቸውና የሥራ ፈጣሪነት ባህል አለመዳበር እንደ አገር ለሥራ ዕድል ፈጠራው ተግዳሮት መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሚኒስቴር መስሪያቤቱ በሥራና ክህሎት፣ ሥራ ስምሪትና ገበያ ዘርፍ የስምንት ወራት የሥራ ዕድል ፈጠራና መንግሥታዊ ድጋፎች እቅድ አፈጻጸም፣ የቀሪ ወራት እቅድ፣ በድጋፍ እና ክትትል ዙሪያ በተገኙ ተሞክሮዎች ዙሪያ ትናንት በደብረ ብርሃን ከተማ መክሯል።

በመድረኩ ንግግር ያደረጉት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን፣ የሥራ ዕድል ፈጠራው ግብርናን፣ ኢንዱስትሪንና የአገልግሎት ዘርፎችን ያካተተ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ሚዛኑ ወደ አገልግሎት ዘርፉ እያዘነበለ እንደሆነ ገልጸዋል። ይህም የሥራ ፈጠራ አስተሳሰብ ባህል አለመዳበርን ያሳያል ነው ያሉት።

ዋነኛ የሥራ ዕድል ፈጣሪ የግሉ ዘርፍ እንደሆነና የመንግሥት ሚና ምቹ ሁኔታን መፍጠር እንደሆነ ተገንዝቦ መሥራት እንደሚገባም አቶ ንጉሡ ተናግረዋል። ዜጎች ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑና መንግሥታዊ ድጋፎችን እንዲያገኙ የሥራ ፈጠራ ባህልን የሚያዳብሩ ስልጠናዎች እየተሰጡ እንዳለም አመላክተዋል። በመላው አገሪቱ ከሦስት ሺህ በላይ ብሩህ ሀሳቦች ተወዳድረው እውቅናና መነሻ ካፒታል የሚሰጥበት ሥርዓት መጀመሩንና ይህም የበጀት ዓመቱ ሳይጠናቀቅ ተፈጻሚ እንደሚሆን ነው የተናገሩት።

ከዚህም ባሻገር የሥራ ዕድል ፈጠራ ትግበራን መገምገም የሚያስችል «የመረጃ ማጥራት» ጥናት በገለልተኛ አካላት በመላ አገሪቱ እየተጠና እንዳለም ጠቅሰዋል። በተያዘው ዓመት ስምንት ወራት እንደ አገር ሁለት ሚሊዮን 692ሺ 268 የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታስቦ ሁለት ሚሊዮን 84ሺህ 702 ወይም የእቅዱን 77 በመቶ ማሳካት እንደተቻለ አስረድተዋል።

የሥራ ዕድል ፈጠራው ላይ ዓለም አቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ተፅዕኖ የሚያሳድሩ መሆናቸውን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ዘርፉ ሰላምና ኢንቨስትመንትን የሚሻ ጉዳይ ነው። ወቅቱ የተለያዩ ዓለም አቀፋዊና አገራዊ ችግሮች ጐልተው የሚታዩበት ጊዜ ቢሆንም በሥራ ዕድል ፈጠራ በኩል ባለፈው ዓመት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር የሚበረታታ ውጤት ተመዝግቧል ብለዋል። በሥራ ዕድል ፈጠራው አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሚያና አዲስ አበባ የተሻለ አፈጻጸም ነበራቸው።

የደብረብርሃን ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ በድሉ ውብሸት በበኩላቸው፣ በከተማዋ በዚህ ወቅት በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ ከ560 በላይ ኢንዱስትሪዎች እንዳሉ ጠቅሰው፣ ወደ ሥራ በገቡት ከፊል ኢንዱስትሪዎች ለ25 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን አስታውቀዋል።

በቀጣይም ሁሉም ኢንዱስትሪዎች ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ ሲገቡ ከ100 ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል እንደሚፈጠረ ተናግረዋል። የሥራ ፈጠራ ባህል አለመዳበር፣ የገበያ ትስስር፣ የመሬትና ብድር አቅርቦት የዘርፉ ተግዳሮቶች መሆናቸውን የጠቆሙት አቶ በድሉ፤ መንግሥት በሚጠበቀው ደረጃ ድጋፉን እንዲያጠናክርም መክረዋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በያዝነው ዓመት 3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ያህል ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው አቅዶ እየሠራ እንደሚገኝ በመድረኩ ተገልጿል።

## የሃይማኖት ተቋማት የማኅበረሰብ ችግርን የሚፈቱ ተግባራትን በስፋት ማከናወን እንደሚገባቸው ተገለጸ

**ኤፍሬም አንዳርጋቸው**

ሐዋሳ፡- የሃይማኖት ተቋማት ከሚሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎት በተጓዳኝ የኅብረተሰቡን ችግር የሚፈቱ ተግባራትን በስፋት እና በጥራት መሥራት ይኖርባቸዋል ሲሉ የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ ገለፁ።

ርዕሰ መስተዳድሩ ከብፁዕ ካርዲናል ብርሃነ ኢየሱስ ሊቀጳጳስ ዘ ካቶሊካዊያን እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በሐዋሳ ከተማ ከ324 ሚሊዮን ብር በላይ ማስፋፊያ ግንባታ የተደረገለትን የቡሹሉ የእናቶች እና ሕፃናት ልዩ የሕክምና ማዕከል መርቀው ለአገልግሎት ክፍት አድርገዋል።



አቶ ደስታ ሌዳሞ



ዶክተር ሰላማዊት መንገሻ



ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነኢየሱስ ሊቀጳጳስ ዘ ካቶሊካዊያን

በወቅቱ የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ እንደገለጹት፤ የሃይማኖት ተቋማት ዜጎችን ለዘላለማዊ ሕይወት ከማዘጋጀት ባለፈ በምድራዊ ኑሯቸው እንዳይቸገሩ በጤና፣ በትምህርት እና በማኅበራዊ ዘርፎች ማገዝ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ዓለም አቀፍ ልምድና ተሞክሮን መሠረት በማድረግ እናቶች እና ሕፃናት ተገቢውን የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ይህ ሆስፒታል እንዲገነባ በማድረጓ ለክልሉ ብቻ ሳይሆን ለአገር ውስጥ የጤና ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ መሆን የሚችል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በቀጣይም መሰል የሃይማኖት ተቋማት የሚሰጧቸውን ማኅበራዊ አገልግሎቶች አጠናክረው እንዲቀጥሉ የክልሉ መንግሥት አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ያደረጋል ሲሉ ገልፀዋል።

የሲዳማ ክልል ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሰላማዊት መንገሻ በበኩላቸው፤ ተቋሙ ደረጃውን ጠብቆ እና በዘመናዊ ቁሳቁስ እንዲደራጅ መደረጉ ለክልሉ ብቻ ሳይሆን ለአጎራባች ክልሎች ዘመናዊ ሕክምና ለመስጠት ያስችላል ነው ያሉት።

ማዕከሉ በዘመናዊ መልክ መገንባቱ፣ ዘመኑ በደረሰበት የሕክምና መሣሪያዎች መደራጀቱ፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት የሰው ኃይል ማሟላቱ ለሌሎች መንግሥታዊ የሕክምና ተቋማት እውቀት፣ ክህሎትንና ልምድን ለማሸጋገርም ያግዛል።

በተለምዶ ሎቄ ተብሎ የሚታወቀውና በጤና ጣቢያ ደረጃ አገልግሎቱን የጀመረው የሕክምና ማዕከሉ አሁን ላይ የላቀ የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉ ቤተክርስቲያኗን የሚያስመሰግን እንደሆነ ጠቅሰው፣ ማዕከሉ የእናቶች እና ሕፃናትን ሞት ለመቀነስ የሚደረገውን ክልላዊና አገራዊ ጥረት የሚያግዝ መሆኑን ዶክተር ሰላማዊት ገልጸዋል።

ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነኢየሱስ ሊቀጳጳስ ዘ ካቶሊካዊያን እንደተናገሩት፣ በኢትዮጵያ ባህላዊ ሕክምና ለረዥም ጊዜ ሲተገበር ቢቆይም ዘመናዊ የሕክምና አገልግሎት ግን በሚፈለገው መጠን እና ደረጃ እያደገ አይደለም። በመሆኑን በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከ324 ሚሊዮን ብር በላይ የማስፋፊያ ግንባታ የተደረገለትን የቡሹሉ የእናቶች እና ሕፃናት ልዩ የሕክምና ማዕከል የግንባታውን ወጪ በመሸፈን ለአገልግሎት ክፍት አድርጋለች ሲሉ አብራርተዋል።

የቡሹሉ እናቶች እና ሕፃናት ልዩ ሕክምና ማዕከል በሐዋሳ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ስር ከሚገኙ 13 የጤና ተቋማት መካከል አንዱ መሆኑን ተናግረዋል። ይህም የአካባቢው ኅብረተሰብ ደረጃውን የጠበቀ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኝ እንደሚያስችለው ጠቅሰው፤ በቀጣይም ከፌዴራል መንግሥት፣ ከክልሉ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ተመሳሳይ ሥራ እንሠራለን ብለዋል።

የቡሹሉ የእናቶች እና ሕፃናት ልዩ የሕክምና ማዕከልም ከ44 ዓመታት በፊት ባልተደራጀ ሁኔታ የጤና አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1979 በጤና ጣቢያ ደረጃ ሕክምና መስጠት እንደጀመረ ከማዕከሉ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።



## የስንብት የአገልግሎት ክፍያ አልተሰጠንም ሲሉ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ሠራተኞች ቅሬታቸውን አሰሙ

### - የደረሰበትን ዝርፊያ አጣርቶ ሲያጠናቅቅ ተገቢውን ክፍያ እንደሚፈጽም ፋብሪካው አስታውቋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የማስጠንቀቂያና የስንብት ደብዳቤ በወቅቱ ቢሰጠንም በሕግና በሥርዓቱ መሠረት የስንብት የአገልግሎት ክፍያ አልተሰጠንም ሲሉ የፋብሪካው ሠራተኞች ገለፁ። በፋብሪካው ላይ የተፈጸመው ዝርፊያ ተጣርቶ ሲጠናቀቅ የአገልግሎት ክፍያቸውን እንደሚያገኙ ፋብሪካው አስታውቋል።

በተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የውሃ አቅርቦት ቡድን መሪ አቶ ሽመልስ መገርሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ፋብሪካው የስንብት ደብዳቤ ከሰጣቸው ሁለት ወር አልፏቸዋል። ነገር ግን በስንብት ደብዳቤው ሕግና ሥርዓት መሠረት የአገልግሎት ክፍያ አልተሰጣቸውም። በዚህም ቤተሰባቸው እና የሚደግፏቸው ሰዎች ለከፍተኛ ችግርና ለርሃብ እየተዳረጉ ነው። ስለዚህ ፋብሪካው በሠራተኛው ላይ እየደረሰ ያለውን ችግር ተረድቶ ጉዳዩን ሊፈታ ይገባል ብለዋል።

ሌላው የፋብሪካው ሠራተኛ አቶ ሽመልስ ደምሌ በበኩላቸው፤ ከፋብሪካው የስንብት ደብዳቤ ከተሰጠኝ በኋላ የአገልግሎት ክፍያ ከሁለት ወር በላይ ባለማግኘቴ አስቸጋሪ ሕይወት እየመራሁ ነው ሲሉ ቅሬታቸውን ተናግረዋል። በተለይ አካባቢው በረሃ በመሆኑ ከሌላ አካባቢዎች በተለየ ሁኔታ ቤተሰብን ማስተዳደር ይከብዳል ነው ያሉት።

አንድ ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሲሰናበት የአገልግሎት እና የሥራ መፈለጊያ ክፍያ ሊከፈለው እንደሚገባ ያነሱት ሠራተኛው፤ ከዚህ ባለፈ ደግሞ ሠራተኛ ያልወሰደው አንዳንድ ጥቅማጥቅም ሊሰጠው እንደሚገባ ሕጉ ይደነግጋል። ነገር ግን የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ እስከ አሁን በሕጉ መሠረት እየሠራ አይደለም ያሉት ቅሬታ አቅራቢው፤ ሠራተኛው የአገልግሎት ክፍያውን ባለማግኘቱ ከባድና አስቸጋሪ ሕይወት እየመራ ነው ሲሉ ገልጸዋል። ስለዚህ ጉዳዩ የአንድ ሰው ሳይሆን ብዙዎቹን የሚመለከት በመሆኑ የሚመለከተው አካል ጉዳያችንን ተረድቶ በአስቸኳይ እንዲፈታልን እጠይቃለሁ ብለዋል።

በዚሁ ጉዳይ ዙሪያ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ የሰው ሀብት አመራርና ማኔጅመንት አስተባባሪ አቶ የውልሰው እጅጉ በሰጡት ምላሽ፤ የስንብት ደብዳቤ የተሰጣቸው አንድ ሺህ 280 ሠራተኞች የጠየቁት ጥያቄ ተገቢ እንደሆነ ገልጸዋል።

እስካሁን ፋብሪካው ለሠራተኞቹ ተገቢውን የማሰናበቻ የአገልግሎት ክፍያ እንዳልሰጣቸው የተናገሩት ኃላፊው፤ ይህ የሆነው በፋብሪካው ላይ የተፈጸመ ዝርፊያ በመኖሩ እንደሆነና ዝርፊያው ተጣርቶ ሲጠናቀቅ ሠራተኞቹ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ያገኛሉ ብለዋል። ይህንን ጉዳይ ትኩረት አድርጎ የሚሠራ ቡድን እንደተቋቋመ ተናግረው፤ የሠራተኞቹ ቅሬታ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚፈታ ተናግረዋል።

## ኢትዮ ቴሌኮምና ሳምሰንግ ኩባንያ ተንቀሳቃሽ ስልኮችን ለማቅረብ ስምምነት ፈጸሙ

### - ኩባንያዎቹ አዲሱን የሳምሰንግ ጋላክሲ ስልክ ለገበያ ማቅረባቸውን አብስረዋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም እና ሳምሰንግ ኩባንያ ለደንበኞች የተለያዩ የሳምሰንግ ጋላክሲ ተንቀሳቃሽ ስልኮችን በአጋርነት ለማቅረብ የሚያስችል ስምምነትም ፈጸሙ። ኩባንያዎቹ በአጋርነት አዲሱን የሳምሰንግ ጋላክሲ ኤስ 23 አልትራ ተንቀሳቃሽ ስልክ ለደንበኞች ማቅረባቸውን ትናንት በተካሄደው የማብሰሪያ መርሃ ግብር ላይ ይፋ አድርገዋል።

በማስተዋወቂያ መርሃ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢትዮ ቴሌኮም ቺፍ ማርኬቲንግ ኦፊሰር አቶ ሰይድ አራጋው እንደገለጹት፤ ጋላክሲ ኤስ 23 አልትራ (Galaxy S23 Ultra) ተንቀሳቃሽ ስልክ እጅግ ዘመናዊ ሲሆን በ140 ሺህ ብር ለሽያጭ ቀርቧል።

ደንበኞች ተንቀሳቃሽ ስልኩን ሲገዙ 11 ሺህ 300 ብር ዋጋ ያለው የጋላክሲ በድስ ሁለት በነፃ እንደሚሠጣቸው እና የሦስት ወር ያልተገደበ ዳታ በነፃ እንደሚያገኙም ተገልጿል።

የጋላክሲ ኤስ 23 አልትራ ግራፊክስ አፈጻጸም ከ40 በመቶ በላይ ፍጥነት ያለው ሲሆን የአፈጻጸም አቅሙን መጠን በማሻሻል ለፎቶግራፍ እና ለቪዲዮግራፊ እጅግ ፈጣን ለሆነ የጌም እይታ እና ለመሳሰሉት አፈጻጸሙንና እና የኃይል ፍጆታውን ማመጣጠን ያስችላል።

ጋላክሲ ኤስ 23+ እና ጋላክሲ ኤስ 23 ተንቀሳቃሽ ስልኮች አቅርቦት በኢትዮጵያ በመርሃግብሩ ይፋ ተደርጓል። ጋላክሲ ኤስ 23 ፕላስ (Galaxy S23 + (8/256 GB) በብር 105 ሺህ እና ጋላክሲ ኤስ 23 በብር 95 ሺህ ዋጋ ለሽያጭ የቀረቡ ሲሆን ተንቀሳቃሽ ስልኮቹን ለሚገዙ ደንበኞች አንድ ሺህ 200 ብር ዋጋ ያላቸው ሲሊከን ሽፋን በነፃ ይሰጣቸዋል።

ለሽያጭ የቀረቡት ተንቀሳቃሽ ስልኮች የሃያ አራት ወራት ዋስትና ያላቸው ሲሆን ሳምሰንግ ኬር + በተንቀሳቃሽ ስልኮቹ አገልግሎቶች ላይ ድንገተኛ ጉዳት እንዳይደርስ ጥበቃ መደረጉን ያረጋግጣል። አዳዲሶቹ ተንቀሳቃሽ ስልኮች በኢትዮ ቴሌኮም የሽያጭ ማዕከላት ለሽያጭ መቅረባቸውም ተገልጿል።

# አትክልትና ፍራፍሬ እንዳይበላሽ የሚረዳ ማሸጊያ ማሽን ወደ ሥራ ይገባል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የአትክልትና ፍራፍሬ ማሸጊያ ማሽን በተያዘው በጀት ዓመት ወደ ሥራ የሚገባ መሆኑን የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ምህዲን አስፋው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቄራ ላይ ሁለት የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የስኳር ምርት ማሸጊያ ማሽኖች የመትከል ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የመስመር ዝርጋታ ሥራዎች በማሟላት በተያዘው በጀት ዓመት ወደ ሥራ ይገባል።

በስድስት ሚሊዮን ብር ወጪ የሚገነቡት የአትክልትና ፍራፍሬ ማሸጊያዎች ምርት እንዳይበላሽና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ታሽጎ እንዲቀመጥ ይረዳሉ ያሉት ኃላፊው፣ በቀጣይ የሚገነባው የአትክልትና ፍራፍሬ የማቀዝቀዣ መጋዘን ሕንፃ ሲጠናቀቅ ደግሞ የተሻለ ጥራት ያላቸውን ምርቶች ለገበያ ለማቅረብ ይረዳል ብለዋል።

እንደ አቶ ምህዲን ገለጻ፤ ምርቶቹ ታሽገው ሲሸጡ በኅብረተሰቡ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ተደርጎ የተለያዩ ኬሚካሎች የሚቀቡ በመሆኑ የአቅርቦት ችግርን ከመቀነስ በተጓዳኝ ከውጭ አገራት ታሽገው የሚገቡ ምርቶችን በማስቀረት በአገሪቱ ላይ የወጪና ገቢ ንግድ ለማመጣጠን ይረዳል። በተጨማሪም የፍራፍሬና የስኳር ማሸጊያ ማሽኖቹ ለብዙ ጊዜ አስቀምጠን በሱቆቻችን ከመሸጥ በተጨማሪ አሽገን ለሱፐር ማርኬቶች ለማከፋፈል ምቹ አጋጣሚን ይፈጥራል።

ማሸጊያ ማሽኖቹ እና የማቀዝቀዣ መጋዘን ሥራቸው ተጠናቆ ወደ ሥራ በሚገቡበት ጊዜ የአገር ውስጥ ገበያን ከማረጋጋት በተጨማሪ የወጪ ንግድን በማሳደግ ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝ ነው ያሉት አቶ ምህዲን፤ ብክነትና ብልሽትን ለመቀነስ እንዲሁም በአገሪቱ ያለውን የዋጋ ግሽበት ለመቀነስ ያለው ሚናም የጎላ መሆኑን ጠቁመዋል።


አቶ ምህዲን አስፋው

አቶ ምህዲን አክለውም፤ የሌማት ትሩፋት ፕሮጀክት መጀመሩ ለአምራቹም ሆነ ለተጠቃሚው የአቅርቦት ችግርን ከመፍታትና ገበያውን ከማረጋጋት አንጻር ትልቅ ዕድል የሚፈጥር ነው። ብርቱካን፣ ሙዝ፣ አቮካዶ፣ ማንጎ እና ሌሎች ፍራፍሬዎች እንዲሁም ቲማቲምና ድንች በአትክልት ዘርፍ በዋናነት ያከፋፈልናቸው ምርቶች ናቸው ብለዋል። ኮርፖሬሽኑ ለንግድ ከተቋቋሙ የግብርና የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በጋራ እየሠራ ነው። በተቋማቱ መካከል የገበያ ትስስር መፈጠሩ ማህበራቱን በማበረታታት ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር አግዟል።

ለመንግሥት በተለይ የአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፉን ከማበረታታት አንጻር በፖሊሲም ይሁን ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም ጣልቃ ገብቶ አምራቾችን ማበረታታትና ኤክስፖርቱን በማስተዋወቅ እገዛ እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

# ከኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ከ48 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

*መክሊት ወንድወሰን*

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሰባት ወራት ከኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ከ48 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ።

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ወደ ሱዳን፣ ጅቡቲ እንዲሁም በቅርቡ ወደ ኬንያ የኤሌክትሪክ ኃይል በመላክ ከኤሌክትሪክ ሽያጭ ከ48 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል።

በዚህም በሰባት ወራት የኤሌክትሪክ የኤክስፖርት ዕቅድ ውስጥም 81 ነጥብ ስምንት በመቶ ማሳካት መቻሉን ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ ከአምስት ሺህ 200 ሜጋ ዋት በላይ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ላይ እንደደረሰች የተናገሩት አቶ ሞገስ፤ በመጪዎቹ ጊዜያትም ወደ ታንዛኒያ፣ ደቡብ ሱዳን እና ሶማሌላንድ ለመላክ መግባባት ላይ መደረሱን ገልጸዋል።

እንደ ኮሙዩኒኬሽን ኃላፊው ገለጻ፤ ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል የማምረትና ኤክስፖርት የማድረግ አቅም አላት። በመሆኑ አንዳንድ የአፍሪካ አገራት አገልግሎቱን ከኢትዮጵያ ለማግኘት ያላቸውን ፍላጎት አሳይተዋል። ኢትዮጵያ ፍላጎት ካሳዩና ሌሎች አገራት ጋር በመተባበር የኤሌክትሪክ ኤክስፖርት አቅሟን ለማስፋት ጥረት ስታደርግ ቆይታለች።

በቀጣይ አስርት ዓመታት የጎረቤት አገራትን የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት ማሟላት ከተቻለ ከኤክስፖርት ከፍተኛ ገቢ ከሚገኝባቸው ምርቶች መካከል የኤሌክትሪክ ሽያጭ አንዱ መሆን ይችላልም ነው ያሉት።

ከኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ጋር በተያያዘ ሱዳን የኤሌክትሪክ የክፍያ ዋጋን ከመክፈል ጋር የተወሰነ ክፍተት እንደነበረባት የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ ክፍተቱ ከአገሪቷ የውስጥ ችግር ጋር ተያይዞ የመጣ ነው ብለዋል። ችግሩን መንግሥት ጣልቃ ገብቶ ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ገልጸው፤ በሱዳን በኩል የተወሰነ ጊዜ እንዲሰጣቸው መጠየቃቸውን አቶ ሞገስ ተናግረዋል።

# ለ2015/16 ምርት ዘመን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ተከማችቶ ከሚገኘው ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያም ውስጥም 710 ሺህ ኩንታል ማዳበሪያ ለዘንድሮ በጋ መስኖና የበልግ ምርት ወቅት መጠቀም መቻሉን ተናግረዋል።

የአፈር ማዳበሪያው በፍጥነትና በተቀናጀ ሁኔታ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ እንደሚገኝ አመልክተው፤ የቀረውን ማዳበሪያ ቶሎ ወደ አርሶ አደሩ እንዲደርስ በቅርበት እየተከታተለ ነው፤ ግብርና ባለሙያዎችና ክልሎችም እየቀረበ ያለውን ማዳበሪያ ቶሎ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ማድረግ እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል።

አርሶ አደሩ ከአፈር ማዳበሪያ ከመጠቀም ባሻገርም የተፈጥሮ ማዳበሪያን በመጠቀም ረገድ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚኖርበት ገልጸዋል። በኮቪድ፣ በነዳጅ ዋጋ መጨመርና በሩሲያና ዩክሬን ጦርነት ምክንያት የግብርና ግብዓቶችና መሣሪያዎች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ መኖሩን አውስተው፤ ይህም በግብርና ግብዓት አቅርቦት ላይ ጫና መፍጠሩን ነው የተናገሩት።

በሌላ በኩልም 2015/16 የምርት ዘመንም ወደ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርጥ ዘር ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ ዕቅዶ እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ከዚህ ውስጥ 370ሺ ኩንታል ምርጥ ዘር የፌዴራል የምርጥ ዘር አቅራቢ ተቋማት የሚቀርብ መሆኑን አመልክተዋል። ቀሪውን ክልሎች በሚያባዙት የምርጥ ዘር የሚሸፍኑት ነው ብለዋል።

በምርት ዘመኑም አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሊትር የተለያዩ ጸረ ተባይ ኬሚካሎችን ለማቅረብ እየተሠራ መሆኑን ዶክተር ግርማ ጠቁመው፤ እስካሁን በተሠራው ሥራም በአሁኑ ጊዜ 970ሺህ ሊትር የሚሆኑ ለግብርና የሚውሉ ኬሚካሎች ወደ አገር ውስጥ መግባታቸውን ጠቅሰዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ መንግሥት በግብርናው ዘርፍ የተገኘውን ለውጥ ለማስቀጠል የተለያዩ ድጋፎችን ሲያደርግ ቆይቷል። ከእነዚህ መካከል የግብርና ግብዓቶችን ተደራሽ ለማድረግ የግብርና መሣሪያዎች ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ እየገቡ ናቸው። ይህን ዕድል በመጠቀም የፋይናንስ ተቋማት በብድር የግብርና ግብዓቶችንና ማሽነሪዎችን ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እንዲያደርጉ በተሠራው ሥራም ትራክተሮች፣ ኮምባይነሮች፣ የውሃ መሳቢያ ሞተሮች ለአርሶ አደሩ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲደርሱ ተደርጓል። ስንዴም ከውጭ ከማስገባት በበጋ ስንዴ ልማት በአሁኑ ጊዜ የአገር ውስጥ ፍላጎትን ሙሉ ለሙሉ በመሸፈን ለውጭ ገበያ መቅረብ መቻሉን ጠቅሰዋል።

# የመዲናዋን ኢኮኖሚያዊና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አካላትና ሕዝቡን በማሳተፍ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ማከናወን ተችሏል። የመዲናዋን ሰላም አስተማማኝ ለማድረግ ሕዝቡን ያሳተፈ የሰላም ሰራዊት በማደራጀትና የፖሊስ ኃይል በማጠናከር ረገድ ውጤታማ ሥራ ተሠርቷል።

ሌብነትን በመቆጣጠርና የሕግ የበላይነትን ለማስከበር ብሎም የተጠያቂነት ሥርዓት ለማስፈን ሕዝባዊ ንቅናቄ መደረጉን የገለጹት ከንቲባዋ፤ በከተማ ደረጃ የፀረ ሙስና ንቅናቄ ግብረ ኃይል በማቋቋም የኅብረተሰቡን ጥቆማ መሠረት ተደርጎ 215 አመራሮች፣ ባለሙያዎችና ደላሎች በሕግ ቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው እየታየ ይገኛል ብለዋል።

የመዲናዋን የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ለማዘመን በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት እንዲሰፍን መደረጉን የገለጹት ከንቲባዋ፤ የገቢ ተቋማትም በቴሌ ብር፣ በኢ ታክስ እና በኢ ፋይሊንግ ሥርዓት ገቢ እንዲሰበስቡ ተደርጓል ብለዋል። ንግድ ፈቃድ በኦን ላይን የማደስና በ16 የአገልግሎት ዓይነቶች ከ345 ሺ በላይ የንግዱ ማኅበረሰብን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉንም አብራርተዋል።

የዲጂታላይዝድ ሥርዓት በየካቲት 12፣ በአበበች ጎበና፣ በጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታሎች ሙሉ ለሙሉ የተተገበረ ሲሆን በሌሎች ትልልቅ ሆስፒታሎችና በ15 ጤና ጣቢያዎች በከፊል የዲጂታላይዝድ ሲስተም መተግበር መጀመሩንም ተናግረዋል።

በ15 የምገባ ማዕከላት በቀን 30 ሺህ የሚሆኑ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያሉ ነዋሪዎችን በምገባ ፕሮግራም ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ያወሱት ወይዘሮ አዳነች፤ 600 ሺህ የነበረውን የተመጋቢ ተማሪዎችን ቁጥር በግማሽ ዓመቱ ወደ 700 ሺህ ማደጉን ጠቅሰዋል።

በሥራ ዕድል ፈጠራ ረገድም 246 ሺህ 999 ዜጎች በቋሚነት፣ 37 ሺህ 999 ዜጎች ደግሞ በጊዜያዊነት የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሲሆን ከእነዚህም 143 ሺህ 813 ሴቶች፤ 235 ሺህ 436 የሚሆኑት ደግሞ ወጣቶች ናቸው ብለዋል።

1 ነጥብ 4 ቢሊዮን የተዘዋዋሪ ብድር በመጠቀም 356 ሺህ 761 ኩንታል ጤፍ በሸማች ኅብረት ሥራ ማህበራት በኩል በማቅረብ ገበያ የማረጋጋት ሥራ መሠራቱን የተናገሩት ከንቲባ አዳነች፤ የኑሮ ውድነትን ለመግታት የእሁድ ገበያ በሁሉም ክፍለ ከተሞች በ137 የገበያ መዳረሻዎች በማስፋፋት የግብርና ምርቶች ከአርሶ አደሩ ወደ ተጠቃሚው በቀጥታ እንዲደርሱ ማድረግ እንደተቻለም አመልክተዋል።

የመሠረታዊ ፍጆታ ሸቀጦች ለኅብረተሰቡ በፍትሃዊነት ተደራሽ ለማድረግ 272 ሺህ ኩንታል ስኳር፣ 10 ነጥብ 9 ሚሊዮን ሊትር ፓልም ዘይት፣ 194 ሚሊዮን የሸገር ዳቦ መሰራጨቱን ያብራሩት ከንቲባዋ፣ ከሸገር የዳቦ ፋብሪካ በተጨማሪ የተገነቡት የዳቦ ፋብሪካዎች ቁጥር 25 ማድረስ መቻሉንም አንስተዋል።

እንደ ከንቲባዋ ማብራሪያ፣ ከቀረቡት 230 ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ውስጥ 212 ቅሬታዎች ምላሽ አግኝተዋል። የነዋሪውን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ በ5 ሺህ 388 መዝገቦች ላይ ክርክር ተደርጓል። በ995 መዝገቦች ላይ ውሳኔ በመስጠት 877 መዝገቦች ለመንግሥትና ለሕዝብ ተወስነዋል። በዚህም ከ386 ሚሊዮን ብር በላይ የመንግሥትና የሕዝብ ጥቅም ማስከበር ተችሏል። ከቱሪዝም ዘርፉም 3 ነጥብ 1 ሚሊዮን የውጭ እና 224 ሺህ የአገር ውስጥ ጎብኚዎችን በማስተናገድ ከውጭ አገር ጎብኚዎች ብቻ 13 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ገቢ ተገኝቷል።

ኑሮ ውድነትን መቆጣጠር፣ የሕግ የበላይነትን ማስፈን፣ አማራጭ የመኖሪያ ቤቶችን ማቅረብ፣ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በይበልጥ ተደራሽ ማድረግ እና ሌብነትን መታገል ቀጣይ የከተማ አስተዳደሩ አቅጣጫ እንደሆኑ ከንቲባ አዳነች አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በኢትዮጵያዊ የመተሳሰብ ባሕልና አንድነት በድርቅ የተጎዱ ወገኖቻችንን እንታደግ!

ኢትዮጵያውያን መልከ ብዙ ፤ ዓይነተ ልዩ ልዩ ነን። የተለያየ ሃይማኖት፣ ባሕልና እምነት ያለን፣ ባለብዙ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦችም ነን። እንደ መልክዓምድሩ አቀማመጥ እንደየክልሎቻችን ስፋትና ዓይነት ተፈጥሮ የለገሰችን በርካታ ገጸ በረከቶችም አሉን። እነዚህን ሁሉ ገጸ በረከቶች የምንቋደሰው በመተሳሰብ፣ በመተባበርና በአንድነት ሆነን ነው። ደስታና ኃዘናችንን የምንካፈለው፤ ችግሮቻችንን በጋራ የምናሳልፈው በመረዳዳትና በመተሳሰብ ባለን ኢትዮጵያዊ ባሕላችን ነው። ይሄ የኢትዮጵያዊነታችን መገለጫ አንዱ ምልክታችን ነው።

በጀግንነትም ዓለም የመሰከረው ታሪክ የዘገበው የድል ባለቤቶች ነን። በሀገር ላይ ጠላት እጁን ሲያነሳ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ሆ ብሎ መነሳት የምንታወቅበት የጀግንነት ታሪካችን ነው። ይሄ የጀግንነት መገለጫችን ታዲያ ጠላት ከውጪ ሲመጣ ብቻ የሚገለጽ አይደለም። ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች በሚያጋጥሙ ጊዜም «የወገን ደራሹ ወገን ነው» በሚል ጠንካራ የጀግንነት አቋማችንን እናሳያለን ።

በተለየ ሁኔታ ውስጥ ሆነንም ለተቸገሩ ወገኖቻችን ከአለን ላይ አካፍለን በመስጠት ወገናዊነታችንን በተግባር እናረጋግጣለን። በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ምክንያት የተፈናቀሉና ለችግር የተጋለጡ ወገኖቻችንን በመርዳትና በመደገፍ ፣ በዓላት በመጡ ቁጥር ያለንን ተካፍለን በጋራ በማሳለፍ ብዙ መልካም የሆኑ የመረዳዳት ዘመናትን አሳልፈናል። ኢትዮጵያዊ አንድነታችንን የሚያጠናክሩ ብዙ ብዙ ተግባራትን ከውነናል። አሁንም ይህንኑ የመረዳዳትና የመተሳሰብ ተግባር ቀጥለናል። ወደፊትም አጠናክረን ልንቀጥልበት የሚገባን ነው።

በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት የድርቅ አደጋ ተከስቷል። በተለይ በየ10 ዓመቱ የሚከሰተው የድርቅ አደጋ ጉዳቱ ሰፋ ያለ ስለሚሆን በብዙ መልኩ በሀገር ላይ ፈታኝ ሆኖ አልፏል። ድርቅ በሚከሰትበት ወቅት በተለይም ሕጻናት እና አረጋውያን በሰፊው ተጎጂ ይሆናሉ። የቤት እንስሳት ይሞታሉ።

አሁንም በተለያየ አካባቢ የሚኖሩ ወገኖቻችን ላይ የድርቅ ችግር አጋጥሟል። በዚህም በርካታ ቁጥር ያላቸው ዜጎቻችን ለችግር ተጋልጠዋል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ የቤት እንስሳቶች በድርቁ አደጋ ሞተዋል። በሕይወት ያሉት የወገኖቻችንን ርዳታ እየተጠባበቁ ናቸው። የወገኖቻችን ጉዳት የእያንዳንዳችን ጉዳት ነውና ልንደርስላቸው፣አይዟችሁ፣ አለንላችሁ ልንላቸው ይገባል። ለችግሩ የተጋለጡ ዜጎች የምግብ እህል ፣ ለሕጻናት አልሚ ምግብ ፤ ለቤት እንስሳቶች ደግሞ መኖ እና ውሀ በአስቸኳይ ያስፈልጋቸዋል። ከፊታቸው የተጋረጠባቸውን ችግር ማለፍና መቋቋም የሚቻለው እያንዳንዳችን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ የምንገኝ ዜጎች ለወገኖቻችን ስንደርስላቸው ነው።

ስለዚህ ለችግር የተጋለጡ ወገኖቻችንን ሕይወት ለማትረፍ ዛሬ ሁላችንም ልንረባረብ ይገባል። እስከአሁን ባለው ሂደት በዋናነት መንግሥት እንዲሁም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ እያደረጉ ነው ። አንዳንድ ግለሰቦችም የአቅማቸውን ድጋፍ እያሰባሰቡና እየረዱ ነው። ይሄ በጣም የሚያስመሰግን ተግባር ቢሆንም ካለው ችግር ስፋትና አሳሳቢነት አንጻር ግን በቂ አይደለም። ስለዚህ በተደራጀና በተጠናከረ መልኩ ድጋፍ ማድረግና ለወገኖቻችን አለንላችሁ ልንላቸው ይገባል።

አሁንም ድርቁ በተለያዩ አካባቢዎች ጉዳት ማድረሱን ቀጥሏል። በተለይ አርብቶ አደሮች በሚኖሩባቸው ሰፊ የቤት እንስሳት በሚገኙባቸው አካባቢዎች ችግሩ የገዘፈ ነው። በኦሮሚያ የቦረና ዞንን ጨምሮ በ10 ዞኖች ፣ በሱማሌ በሁሉም ዞኖች እንዲሁም በደቡብ ክልል በደቡብ ኦሞ ዞን ችግሩ በአሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል።

በሶማሌ ክልል ለተረጂነት ከተጋለጡት ከ3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዜጎች መካከል አሁን ላይ እርዳታ እያገኙ ያሉት 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ያህሉ ብቻ ናቸው። አሁንም 2 ነጥበ 4 ሚሊዮን ዜጎች አስቸኳይ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል። እስካሁን ባለው ሁኔታ በዳዋን ብቻ ግመሎችን ጨምሮ 340 ሺህ የሚጠጉ እንስሳት በድርቁ ምክንያት የሞቱ ሲሆን ወደ 600ሺህ የሚጠጉት ደግሞ እጅግ አስጊ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ።

በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በተከሰተው ድርቅ እስካሁን ከ2 ነጥብ 1 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምግብ ቀርቧል። የሕዝቡ የኑሮ መሠረት የሆኑትን የቤት እንስሳት ለመታደግም ውሃ በቦቴ እየቀረበ ይገኛሉ። የፌደራል መንግሥትና ክልሉ 1 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ድጋፍ አድርገዋል። ይሄ ደግሞ መንግሥት ኃላፊነቱን በመወጣት ያደረገው ቢሆንም ከችግሩ ስፋት አንጻር ግን በቂ አይደለም። ሁሉንም ድጋፍ በመንግሥት ብቻ መሸፈንም አዳጋች ነው። በመሆኑ እያንዳንዱ ዜጋ ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፣ በውጪ የሚኖሩ ዲያስፖራዎች ሁሉ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ለወገኖቻችን ልንደርስላቸው ይገባል። ለወገን ደራሽ ወገን መሆኑን በተግባር ማረጋገጥም አለብን!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ይሉኝታን እንደባሕል

ክብረ ነገሥት

ሀገራዊ እሴቶቻችን በርካታ ናቸው። በብዛታቸው ልክም ጥበቃን እያደረጉልን ይገኛሉ። የማንነታችን መሠረትና መለያም በመሆን ዘመናትን እንድንሻገር ያደርጉናል። በትናንት መነጽር ሳይቀር ራሳችንን እንድናየው ያስችሉናል። ዘመናትንም መመልከቻ መነጽሮቻችን ናቸው። « አይ ትናንት ምናልባት ተመልሶ ቢመጣ » ያስብሉናል።

ምክንያቱም ትናንት የባሕል ወረርሽኝ ሳይኖርብን በመቻቻል ነገሮችን አልፈናል። ትናንት ችግር ሲያጋጥመን ተደጋግፈን አሳልፈነዋል። ትናንት የወደቀ ስናይ ጎንበስ ብለን ማንሳት እንጂ እረግጥን መሄድን አናውቅም። ትናንት ለእኔ ሳይሆን ለእኛ ብቻ መለያችን ነው። ይህ የተገነባው ደግሞ በይሉኝታ ባሕላችን መሆኑን ማንም አይክደውም።

ሰው ምን ይለኛል ስንል ጎረቤት እናግዛለን፤ ከጎረቤት እንዳንለያይ የተቻለንን ሁሉ እናደርጋለን። በተለይም ከባሕሉ ላለማፈንገጥ የምናደርጋቸው ነገሮች ብዙ ናቸው። ይህ ደግሞ የሰዎችን ደስታና ኃዘን መካፈልን፤ ለሰዎች በችግራቸው ጊዜ መድረስን ያሰፉልናል። የአቅምን ያህል ማድረግንም ያበረታታልናል። ለራስ ደስታን መፍጠርንም ይጨምርልናል። ሰዎችን ማክበርም የተለየ ልምዳችን ይሆናል።

በይሉኝታ ሰበብ ለሰዎች መድረስን ልምዳችን እናደርጋለን፤ ለሌሎች ደስታም እንጨነቃለን። ሌሎችን እንድናስቀድም እንሆናለንም። ይህ ደግሞ በግል ሕይወታችን ጭምር ይጠቅመናል። ለአብነትም በሌሎች ሰዎች ዘንድ ያለን ተቀባይነትና ትኩረት ከፍተኛ ይሆናል። ሌሎች ስለእኛ እንዲያስቡ ያደርጋል። የውስጥ መረጋጋትንም ይሰጠናል። ከሆነው ሁሉ ደግሞ ያደግንበት ቤተሰብንና ማኅበረሰብን እንድናመሰግንም ያደርገናል። ከሁሉም በላይ ሀገር ወዳድ ዜጋ እንድንሆን የሚያስችለን ነው።

እንደሚታወቀው ማኅበረሰባችን በማንኛውም መንገድ ቢሆን በመረዳዳት፤ ያለንን ለሰዎች በማካፈልና "እሺ ባይነትን" እንደ መልካም ባሕሪያት አድርጎ ይወስደዋል። ይህ ደግሞ የበለጠ የሚጎለብተው ይሉኝታ ያለው ሰው ስንሆን ነው። የእኔ ብቻ የምንል አለመሆናችን ግለኝነትንና እምቢ ባይነታችንን ያርቅልናል።

ይሉኝታ ያለው ሰው የሃሳብ ልዩነቶችንና ግጭቶችን ጭምር የሚያረግብና በመልካም ባሕሪ የሚቃኝ ነው። በዚህም ከሰዎች የሚጠብቀው ምላሽ ምንም አይኖርም። ምላሹ በራሱ ሕይወት ላይ የሚመጣው ለውጥ እንደሆነ ያምናል። የይሉኝታን አረዳድን ግን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይሉኝታ ለምናደርገው ነገር ከስሜት ይልቅ ምክንያታዊነትን ማስቀደምን ይጠይቃል። ለምንድን ነው ይህን ጉዳይ የምፈጽመው? ሰው ምንይለኛል ብዬ ስለፈራሁ? ወይስ ስለሚያስደስተኝ? ወይስ ኃላፊነት ስለሚሰማኝ? የሚሉ ነገሮችን መመለስ ይገባል።

ይሉኝታ በጥበብ መያዝንና መራመድንም ይፈልጋል። በተለይም አሁን ያለንበት ዘመን ላይ ተቀምጠን በቸልታ ከተጓዝንበት ብዙ ዋጋ ያስከፍለናል። ከዚያም አልፎ ቂመኛና በቀለኛ ያደርገናል። የምንተማመንበትን መልካምነት ያሳጣናል። ምክንያቱም ለሰው ብለን እንጂ ለመልካሙ ባሕላችን አስበን አይደለምና ያደረግነው። በዚህም በቀላሉ በአንዳንድ "አጥማጆች" እንያዛለን። መልካምነታችን በመጥፎ ይተረጎምና እንዳንነሳ ሆነን እንወድቃለን። ልባችን የሚራራለትና ሆዳችን የሚያባባው የሰዎች ሁኔታ ቀጥታ ውድቀታችን ይሆናል።

እንደ ርህራሄ ያሉ ጠንካራ ስሜቶች በጥንቃቄ መያዝ አለባቸው። ከምክንያታዊነት ጋር መተሳሰር ይገባቸዋል። ያ ካልሆነ ግን ከፍ ያለ ርህራሄ ስለሚያሳውረን ማስተዋልና ጥበብን ሳንይዝ ዘው ብለን እንድንገባ ያስገድዱናል። ይህ ሆነ ማለት ደግሞ ከይሉኝታ ልናገኝ የምንችለውን ጠቀሜታ ያሳጣናል። ሰውን አለማመን ጭምር እንዲጠናወተን ያደርገናል።

ይሉኝታ እንደሀገር ያለን ተጽዕኖ ፈጣሪ እሴታችን ነው። ትልልቆችን የምናከብርበት፤ ሰዎችን ለመርዳት ያለንን ጽኑ ፍላጎት የምናሳይበት፣ ለተለያዩ ችግሮች ምላሽ የምንሰጥበት፤ ከመልካም ባሕሪያችን በረከቶችን የምናፍስበት። እናም ይህንን ባሕላችንን የሚሸረሽረውን ማንኛውንም ነገር ከሕይወታችን ማስወገድ አለብን። ያ ካልሆነ ግን ይሉኝታ ከሕይወታችንና ከአካባቢያችን የራቀ አይደለምና ኑሯችንን ያመሰቃቅለዋል።

ሁላችንም በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የይሉኝታ ስሜት እንዲሰማን ተደርገን ተቀርጸናል። በዚህም ሰው ስለእኛ የሚለው ነገር፤ ሰው ስለ እኛ የሚያስበው ነገር ያሳስበናል። ብዙ ጊዜ ማድረግ የምንፈልጋቸውን ነገሮች ሰዎች ምን ይሉኛል ብለን ፈርተን ሳናረጋቸው እንቀራለን። ይህ ደግሞ ከመጥፎ ነገር የሚጠብቀን መልካም እሴታችን ነው። ማለትም አነጋገራችን፣ አለባበሳችን፣ ድርጊቶቻችንና ውሳኔዎቻችን በሙሉ ሰው የሚለውን ነገር በመፍራት ተጽዕኖ ስር የወደቁ ናቸው። በዚህም በእነዚህ ነገሮቻችን መልካሙን ጎዳና ብቻ እንድንከተል እንሆናለን።

ለአብነት አንድ ጉዳይ እናንሳ። አንድ ጋዜጠኛ ወደ ሥራ ሲሄድ አለባበሱ የተሻለ የሚያደርገው መሆን ይኖርበታል። ከተዝረከረከ ሥራውም በዚያው ልክ እንደሚሆን ይታሰባል። ስለዚህም ያ እንዳይሆን ሲል ለሰው ብሎ ያለውን አጥቦና ጸድቶ ወደ ሥራው ይሰማራል። በተመሳሳይ አንድ በእድሜ ከእኛ ተለቅ ያለ ሰው አጠገባችን ካለ ንግግራችን፣ አቀማመጣችን ሁሉ ይቀየራል። ለዚያ ሰው ያለን አክብሮትም በሥራችን ይገለጣል። ይህ ደግሞ መልካምነትን ማብዛት እንደሆነ ማንም አይክደውም።

መታዘዛችን ውስጥ ብዙ የይሉኝታ ሀሳቦች አሉ። መታዘዛችን ውስጥ ብዙ የሚጠቀሙ የሚገለገሉ ሰዎች አሉ። ከመታዘዛችን ጀርባ ብዙ የሚድኑ፣ የሚፈወሱና የሚጽናኑ ሰዎች አሉ። ይሄ እንዳይሆን ግን ይሉኝታ ቢስ የሆኑ ሰዎች ይገጥሙናል። በተለይም ዛሬ ላይ ግለኝነት በበዛበት በዚህ ዘመን በቀላሉ የማንመክታቸው ብዙ ችግሮች እያጋጠሙን ይገኛሉ።

እንደእኔ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም ጠባቂም ጠበቃም አያስፈልገውም። ባሕሉ በራሱ የሚያስተዳድረውና ሰውኛ ባሕሪ ያለው ሕዝብ ነው። በዚህ ባህሉ ደግሞ ችግሮቹን ይጋፈጣል፤ መፍትሔ እየሰጠም ይሄዳል። ሰዎችን ለማራመድ እንጂ ለመጣል የሚጣርም አይደለም።

የአንድ ሰው ምርጫ ቃላቶቹ እና ተግባሮቹ ብቻ ሳይሆኑ ሀሳቦቹ፣ ስሜቶቹና ልምዶቹም ጭምር ናቸው። እነዚህ ነገሮች ደግሞ በይሉኝታ ውስጥ በስፋት የሚታዩ ሲሆኑ፤ በራሱ ንቃተ-ሕሊና ውስጥ እንዲገለጥ የሚደረጉ ናቸው። እስከዛሬ ባለው ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ በሕዝቡ ዘንድ ተገልጠዋል፤ መፍትሔ ሆነዋል የሚል ሀሳብ አለኝ።

አላዋቂ እና ለተግባራዊነታቸው የማይታመኑ ሰዎች ብዙ ጊዜ ይሉኝታ የሚለውን ከራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት ጋር ያስተሳስሩታል። አስፈላጊውን ልምድ እንዲዳብርም መንስኤ ይሆናሉ። በጣም ምቹ እድሎች ባሉበት የሕይወት ሁኔታዎች ውስጥ ተቀምጦ እንኳን ግለኝነት እንዲሰማው ያደርጉታል። ይህ ደግሞ መከባበር እንዳይሰፍን በር የሚከፍት ነው። ለሰው ብለን የምናደርጋቸውን ነገሮች እንድንቀንስ ያስገድደናል። በአጠቃላይ ሰዋዊ ባሕሪያችንን ይነጥቀናል። አሁን ያለንበት ዘመንም በዚህ ሁኔታ የተቃኘ ይመስለኛል።

ሰዎች ብዙውን ጊዜ ቁሳዊ እና ቁሳዊ ያልሆኑ ጥቅሞች ያሳሷቸዋል። በአንድ ሰው ፍላጎት ውስጥ በቅርበት ተሳስረውም ስለሌሎች እንዳይጨነቁ ሆነዋል። ውሳኔዎችን ጭምር ስንመለከት ተገቢነት እንደሌላቸው ብናይም መቃወም እንዳንችል ሆነናል። ምክንያቱም ለሰው ብለን የምንጨነቅ አይደለንም። ይሉኝታ ቢስነታችን ተራራ ነክቷል።

የመደሰት ፍላጎት ፣ በሌሎች ኪሳራ የግል ጥቅምን ማጋበስ ፣ አሉታዊ ግብረመልሶች ፤ ወቀሳ መፈለግ ፣ ከሌሎች የመለያየት ስሜት ለአብዛኛዎቹ ሰዎች መመዘኛዎች ሆነው ሲቀርቡ ይሉኝታ ቦታ አይኖረውም። ይህ ደግሞ ተፈጥሯዊ ግንኙነትን ሳይቀር ይሰብራል። ዛሬ እያየን ያለውም ይህንኑ ነው። ግንኙነታችን ከእኔነት አይበልጥም። ስንደራጅ እንኳን የእኔ ወገን ካልን ሰነባብተናል። በዚህም በከባድ ራስ ወዳድነት ዝንባሌዎች እና ፍላጎቶች ውስጥ ወድቀናል።

ማን ሊያወጣን ይችላል ከተባለ መልሱ አንድና አንድ ነው። የቀደመ ባሕላችን መመለስ። ለዚህ ደግሞ ሁልጊዜ ሰዎችን መፍራት ወደ ልባችን ማምጣት ያስፈልገናል። በአክብሮት ውስጥ ያለን መልካም በረከት ማጤንና ለአዕምሯችን መንገር ይገባናል። ሁሉም ነገር ያልፋል። ፍጥረት ሁሉ ያልፋል። እኛ ሰዎችም ብንሆን እናልፋለን።

ከዛሬ ሀያ ሠላሳና አርባ ዓመታቶች በኋላ ብዙዎቻችን ምድር ላይ በሕይወት አንኖርም። ዛሬ ላይ ግን የምናገለግለው ሀሳብና ፈቃድ አለን ማለት ይጠበቅብናል። ያ ደግሞ የይሉኝታ ሰው በመሆን ሲሆን፤ ሁሉም በተሰጠው መክሊት የሚያተርፍበትን መንገድ ያሳየናልና እንጠቀምበት።

## ፍረዱኝ

# «ከ60 ዓመታት በላይ ሠርተን የኖርንበትን ቤት የቀበሌ ቤት ስለሆነ ውል ተዋዋሉ ተባልን»

አቤቱታ አቅራቢዎቹ

ሙሉቀን ታደገ

ክፍል አንድ

የዛሬው «የፍረዱኝ አምድ» ዝግጅታችን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቀድሞው መጠሪያ ስሙ ወረዳ 19 ቀበሌ 57 በአሁኑ መጠሪያው ደግሞ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 በተለምዶ አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ እየተባለ ወደሚጠራው ሰፈር ይወስደናል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 በተለምዶ አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የሚገኙ ከ65 በላይ የሚሆኑ አባወራዎች «በራሳችን ወጪ እና መሬት ላይ የሠራነውን እንዲሁም ከ60 ዓመት በላይ የኖርንበት ቤት ምክንያቱ በውል ባልታወቀ ሁኔታ ቤቱ የመንግሥት ስለሆነ ከአዲስ አበባ ቤቶች ልማት አስተዳደር ጋር የቀበሌ ቤት ኪራይ ውል ተዋዋሉ ተብለን ተገደናል። በራሳችን መሬት እና ወጭ ሠርተን ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ የኖርንበትን ቤት፤ ሕግ ባለበት ሀገር እንዴት ከአዲስ አበባ ቤቶች አስተዳደር ጋር የኪራይ ውል ተዋዋሉ እንባላለን? የኢትዮጵያ ሕዝብም መንግሥት ማኅበረሰቡን እንዲያገለግሉ ባስቀመጣቸው ሹመኞች እየደረሰብን ያለውን በደል ተመልክቶ ይፍረደን » ሲሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አቤት ብለዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ሕዝብም ግራና ቀኙን አይቶ ይፈርድ ዘንድ ዝግጅት ክፍሉ ስለጉዳዩ ከሰዎች እና ሰነድ ያገኛቸውን መረጃዎች እና ማስረጃዎች በጥልቀት መርምሮ የደረሰበትን የክፍል አንድ ዝግጅት እነሆ ብሏል። ቀሪ የምርመራ ዘገባዎችን በቀጣይ ሳምንት ለሕዝብ የምናደርስ ይሆናል።

መልካምን ንባብ ።

### የፋብሪካው አመሠራረት እና ውዝግቡ መነሻ


ፋብሪካው በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በአርመናዊያን እንደተመሠረተ ከሰዎች እና ከሰነድ ያገኘናቸው ማስረጃዎች ያመላክታሉ። ፋብሪካው ሲመሠረትም በአካባቢው አቶ ተሰማ ወልደማሪያም እና ወይዘሮ ይፍቱ ሥራ አብዩ የተባሉ አባወራ ብቻ ይኖሩ እንደነበር ከአካባቢው ሰዎች የተገኙ ማስረጃዎች ያሳያሉ። አርመናውያኑም ፋብሪካውን ለመትከል ከእኚህ አባወራ በአስራ ሁለት ብር እንደገዙት ያካባቢው ሰዎች እና ለፋብሪካው መሬቱን የሸጡት ቤተሰቦች ያስረዳሉ።

ፋብሪካው ወደ ሥራ ሲገባም 65 የሚደርሱ ሠራተኞችን እንደቀጠረ የተለያዩ ማስረጃዎች ያሳያሉ። ይህን ተከትሎ በፋብሪካው ለሥራ የተቀጠሩ ሰዎች ለሥራ ቦታቸው ቅርብ ሰፈር በመምረጥ ግማሾቹ በአነስተኛ ብር ለፋብሪካው መሬት ከሸጡት አባወራ መሬት ገዝተው ቤት ሠሩ። ግማሾቹ ደግሞ ከወቅቱ የእርስት ቢሮ በምሪት መሬት አገኙ። ይሁን እንጂ እነኚህ 65 የሚደርሱ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ሠራተኞች የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ አልበራቸውም ።።


ቀን ቀን ሲወልደው የንጉሡ ዘመን አለቀና የወታደራዊ ደርግ መንግሥት ተተካ። ይህን ተከትሎ የ47/67 አዋጅ ታወጀ። በዚህም በአርመናውያን ስር ይተዳደር የነበረው ፋብሪካ በመንግሥት ተወረሰ።

በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ ቤት ሠርተው ይኖሩ የነበሩ ሠራተኞችም የሠሩት ቤት ተጠብቆላቸው በራሳቸው ሲያስተዳድሩት ኖሩ። አሁን ላይ እነኚህ ሠራተኞች በቤታቸው እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ ተዋልደው በየመኖሪያ ቤታቸው እየኖሩ ይገኛሉ።

ይሁንና በ2002 ዓ.ም ምክንያቱ በውል ባልታወቀ አግባብ ቤቶቹ ሰነድ አልባ ስለሆኑ ብቻ በወቅቱ በአቃቂ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የቤቶች አስተዳደር ኃላፊ በነበሩት ግለሰብ የ65ቱን አባወራ ቤቶች ባለቤት የአልባ የሚባል መታወቂያ ለጠፉባቸው። ይህን ተከትሎ «በአቃቂ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የቤቶች አስተዳደር ኃላፊ ያለምንም ምክንያት ከመሬት ተነስቶ ቤቶቹ የመንግሥት ስለሆኑ የቀበሌ ቤት ኪራይ ውል መዋዋል


ፎቶ-ሐዲስ አብርሃ

አቶ አሰፋ አሳብሴ



ወይዘሮ ጥሩነሽ ወርቁ



አቶ አሥራት አራርሶ

አለባችሁ» ሲሉ አሁን ላይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አቤቱታ ያቀረቡትን ሰዎች አስገደዱ። ይህን ተከትሎ በወረዳ 6 ቤቶች አስተዳዳሪ እና በነዋሪዎቹ መካከል ውዝግብ ተነሳ።

### ከአቤቱታ አቅራቢዎች አንደበት የተሰማው ቅሬታ

አቤቱታ አቅራቢዎቹ በርካታ ቢሆኑም ስለተፈጠረው ውዝግብ በአግባቡ ሊያስረዱ ይችላሉ የተባሉ የተወሰኑ ሰዎችን በቃለ መጠየቅ አካተናል። ከእነኚህ መካከል አቶ አሥራት አራርሶ አንዱ ናቸው ።

አቶ አሥራት አራርሶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የቤት ቁጥር 160 ነዋሪ ናቸው። እድሜአቸው በሃምሳዎቹ አጋማሽ ላይ እንደሚገኝ ያስረዱት አቶ አሥራት፤ ውዝግብ በተነሳበት ቤት ውስጥ ተወልደው ማደጋቸውን እና አሁን ላይም በቤቱ ልጅም ወልደው እየኖሩ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

እንደ አቶ አሥራት ገለጻ ፤ በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ዙሪያ የራሳቸውን ቤት ሠርተው የሚኖሩ 65 የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ሠራተኞች ነበሩ። እነኝህ ሠራተኞች ምንም እንኳን በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ተቀጥረው የሚሠሩ ቢሆንም ይኖሩበት የነበረውን ቤት በራሳቸው ገንዘብ እና ጉልበት የሠሩት ስለነበር ፋብሪካው በደርግ ዘመነ መንግሥት በአዋጅ 47/67 ሲወረስ የፋብሪካው ተቀጣሪ ሠራተኞች ቤቶች ግን አልተወረሱም ነበር። ምክንያቱም በወቅቱ የነበረው አስተዳደር ቤቶቹ በሠራተኞች ገንዘብ እና ጉልበት የተሠሩ መሆናቸውን አረጋግጦ ስለነበረ።

በወቅቱ የነበረው መንግሥት ሁሉን አቀፍ ማጣራት አድርጎ ቤቶች የሠራተኞች የግላቸው መሆኑን ተረድቶ ያልወረሳቸው ቢሆንም በኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥት ግን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የቦታ እና ዲዛይን ኃላፊ ሆነው የተሾሙት ግለሰብ በ24/12/2002 ዓ.ም በክፍለ ከተማው እና በወረዳው የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ለአንዳቸውም ሳያማክር በራሱ ተነሳሽነት ከ60 ዓመት በላይ የኖሩበትን ቤት ባለቤት አልባ በማለትና ለክፍለ ከተማ በማስተላለፍ እንዲሁም ክፍለ ከተማ ደግሞ ለአዲስ አበባ ቤቶች በማስተላለፉ ሳቢያ የወረዳው ቤቶች ልማት አስተዳደር ነዋሪዎችን የቀበሌ ቤት ኪራይ ውል እንዲዋዋሉ የሚል ማስታወቂያ ለነዋሪዎቹ መላካቸውን ይናገራሉ።

ይህን ተከትሎ በወቅቱ በነበሩት ኃላፊ የተወሰነው ውሳኔ እውነታን ያላገናዘበ እና መነሻው ምን እንደሆነ ስለማይታወቅ በራሳችን ገንዘብ እና ጉልበት በሠራነው ቤት የኪራይ ውል ሊዋዋሉ እንደማይችሉ እና አንድ ግለሰብ ከመሬት ተነስቶ ይህን መሰል ውሳኔ እንዴት በግሉ ሊወስን ይችላል? ሲሉ ለክፍለ ከተማው ቤቶች አስተዳደር አቤት ማለታቸውን ያስረዳሉ።

አቤቱታውን ተከትሎ የክፍለ ከተማው ቤቶች አስተዳደርም ስለእነዚህ ቤቶች የሚያውቀው ነገር እንደሌለ እና ግለሰቡ ከመሬት ተነስቶ በግሉ ይህን የመሰለ ውሳኔ መወሰኑ አግባብ ባለመሆኑ ቅሬታቸውን ለክፍለ ከተማው ሥራ አስፈጻሚ እንዲያመለክቱ ተደረገ። ይህን ተከትሎ አቤቱታ አቅራቢዎቹም ለክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ማመልከታቸውን ይናገራሉ።

በወቅቱ የነበሩት የክፍለ ከተማ ቤቶች አስተዳደር ኃላፊም ስለጉዳዩ ለማጣራት በጣም ቀላል ዘዴዎች መኖራቸውን ገልጸው ፤ ቤቶቹ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ መሆናቸውን እና አለመሆናቸውን ለማጣራት ለፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የባለደራ ምክር ቤት እና የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ማኔጅመንት ስለቤቶች የሚያውቁትን ነገር አጣርተው እንዲያሳውቁ የሚል ደብዳቤ እንደሚጽፉ እና እነኝህ መሥሪያ ቤቶች ውዝግብ ያስነሱትን ቤቶች አናውቅም ካሉ በእውነትም ግለሰቡ ሐሰተኛ እና ትክክል ያልሆነ በመሆኑ ይህንን ቦታ ለአቤቱታ አቅራቢዎች እንመልሳለን በማለት ከላይ ለተገለጹት መሥሪያ ቤቶች ደብዳቤ መጻፉን ይናገራሉ።

ይህን ተከትሎ የፕራይቬታዜሽን ኤጀንሲ ስለቤቱ ምንም የምናውቀው ነገር የለም የሚል ምላሽ ሲሰጥ፤ የባላደራ ምክር ቤት ደግሞ ቤቱ ቀድሞ የቤቶች አስተዳደር ቢሆን ኖሮ ቤቱን ድርጅቱ ለእነሱ ያስረክባቸው እንደነበር ነገር ግን አሁን ላይ ቤቶቹን እነሱ እንደማያውቋቸው የሚገልጽ ምላሽ ሰጡ ።

ሌላው ስለጉዳዩ እንዲያብራራ የተጠየቀው ደግሞ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ማኔጅመንት ነበር። የክፍለ ከተማው መሬት ማኔጅመንትም ስለቤቶቹ የሚያውቀው ነገር እንደሌለ በደብዳቤ ለክፍለ ከተማው ቤቶች አስተዳደር አሳወቀ።

ከዚህ በተጨማሪ የቀድሞው አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ የአሁኑ ኢትዮጵያ ሌዘር ስለጉዳዩ ተጠይቆ ለሠራተኞች የመብራት እና የውሃ ክፍያ ከመክፈል ውጭ ስለቤቶቹ የሚያውቀው ነገር እንደሌለ በደብዳቤ ምላሽ ተሰጠ።

የክፍለ ከተማው ቤቶች አስተዳደርም እነኝህን ደብዳቤዎች ካሰባሰቡ በኋላ ከደብዳቤዎቹ የተገኙ ቀን እና ቁጥሮችን በመጥቀስ «ይህ ቤት የመንግሥት ነው ተብሏል። ስለዚህ ጥያቄአችሁ በቂ መልስ የሚያሰጥ ሆኖ አላገኘንም» ሲሉ እንደመለሱላቸው አቤቱታ አቅራቢዎቹ ይናገራሉ።

ይህን ተከትሎ ጉዳዩን በይግባኝ በ2006 ዓ.ም ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በቅሬታ ሰሚ አቀረቡ። ይሁን እንጂ የክፍለ ከተማው ቅሬታ ሰሚ ይህን ቅሬታ አልቀበልም ይላሉ። ምክንያቱም ቅሬታ ሰሚ ኃላፊ የነበሩት ሰው ቀደም ሲል ችግሩን ከፈጠረው የወረዳ 6 ቤቶች አስተዳደር ጋር በአንድ ቦታ ይሠሩ ስለነበር መሆኑን አመላክተዋል። ይህን ተከትሎ ቅሬታ ሰሚ ቢሮ ቅሬታቸውን ሊቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑን ጠቅሰው ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቤት አሉ።በክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አስገዳጅነት ክፍለ ከተማው ቅሬታ ሰሚ ጽሕፈት ቤት በግድ አቤቱታቸውን እንዲቀበል ሆነ።

ይሁን እንጂ የአቤቱታውን ምላሽ ቀጥታ ለቅሬታ አቅራቢዎቹ መስጠት ሲገባቸው ጉዳዩን ወደ አዲስ አበባ ከተማ ቅሬታ ሰሚ እንዲላክ አደረገ።ይህም የአሠራር ሂደቱን ያልተከተለ ከመሆኑም ባሻገር ሆን ተብሎ ጉዳዩን ለማወሳሰብ የተደረገ ተግባር መሆኑን አቤቱታ አቅራቢው ያስረዳሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቅሬታ ሰሚ የነበሩትም በወቅቱ አጣሪ ኮሚቴ አደራጅተን ስለጉዳዩ ምርመራ እንጀምራለን ብለው እንቅስቃሴ ከጀመሩ በኋላ ምክንያቱ በውል ባልታወቀ አግባብ የጀመሩትን ምርመራውን አቁመው የደረሰበትን የመጨረሻ ምላሽ ነው በማለት ወረዳው ላይ የነበረውን ምላሽ ሳይጨምሩ እና ሳይቀንሱ እንደወረደ አቤቱታ አቅራቢዎቹ ምላሽ እንደሰጧቸው ይገልጻሉ።


ቅሬታ አቅራቢዎችም እውነታን ይዘን እያለ በአንድ ግለሰብ በተፈጠረ የክፋት አካሄድ ስለምን እንዲህ ያለ መልስ እንሰጣለን ? ሲሉ መጠየቃቸውን እና ከተማ አስተዳደሩ ቅሬታ ሰሚም «መንግሥት ከሚቀየመን እናንተ ብትቀየሙ ይሻላል ፤ ሲደክማችሁ ትተውታላችሁ» የሚል በማስፈራራት እና ማንጓጠጥ በተቀላቀለበት አግብብ ትክክለኛ እና ተገቢ ያልሆነ ምላሽ እንደሰጣቸው ያስረዳሉ።

ይህንን የደረሰባቸውን አስተዳደራዊ በድል እንዲፈታላቸው እስከዛሬዋ ቀን ድረስ የተለያዩ የመንግሥት ቢሮዎችን ቢያንኳኩም ምላሽ ማግኘት እንዳልቻሉ ይናገራሉ።

እነኝህን ክርክሮች መከራከር ከጀመሩ አንስቶ እስከዛሬዋ ቀን ድረስ ከአቃቂ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ቤቶች አስተዳደር ጋር ምንም አይነት የኪራይ ውል አልገቡም። ምንም የተጣራ ነገር በሌለበት እያንዳንዱ አባወራ የኪራይ ውል መግባት አለባችሁ በማለት እና በማስፈራራት ቢሞክሩም እስከዛሬ ማንም ሊቀበለው ያልቻለ ነገር ነው።ቤቱ የግላቸው ስለሆነ በምንም አይነት አግባብ የኪራይ ውል ሊገቡ እንደማይችሉ አመላክተዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ቤቱ የቀበሌ ሳይሆን የራሳችን ነው ብለው አቤቱታ አቅርበው ሲከራከሩ ከነበሩ ሰዎች መካከል ምክንያቱ በውል ባልተገለጸ አኳኋን መሬቱን በሰነድ አልባ ተፈቅዶላቸው ግማሾቹ ከክፍለ ከተማው ሕጋዊ ካርታ ሲሰጣቸው፤ የተወሰኑ ሰዎች ደግሞ የአፈር ግብር እንዲከፍሉ በማድረግ ክፍለ ከተማው ስለሰዎቹ ሕጋዊነት እውቅና እንዲኖረው መደረጉን

# ፍረዱኝ




የሲአይ ኤስ መረጃ



አቶ ሳምሶን ይልማ



ወ/ሮ ወይንሸት ለማ

አመላክተዋል።

ለአብነት ያህል እነ ተስፋዬ ዘውዴ 101 የቤት ቁጥር ካርታ የተሰጣቸው ፤ የቤት ቁጥር 102 በላይነህ ጥላሁን የአፈር ግብር የሚከፍሉ፣ የቤት ቁጥር 103 ጋዲሴ ሙለታ ካርታ የተሰጣት እና ግብር እየከፈለች ያለች ፤ የቤት ቁጥር 141 የአፈር ግብር የሚከፍሉ ፤ የቤት ቁጥር 144 የአፈር ግብር የሚከፍሉ ፤ የቤት ቁጥር 145 የአፈር ግብር የሚከፍሉ ፤ የቤት ቁጥር 149 «ለ» የአፈር ግብር የሚከፍሉ፣ የቤት ቁጥር 154 እና 165 የአፈር ግብር የሚከፍሉ ሲሆን ፤ በፕሮስ ካውንስል ጉዳያቸው እየታየላቸው እና በሰነድ አልባ በወጣው መመሪያ መሠረት የቤት ካርታ ሊሰጣቸው በሂደት ላይ የሚገኙ ናቸው ።

እነኝህ ሰዎች ከአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ሠራተኞች ጋር ቤታችሁ የመንግሥት ስለሆነ አዲስ አበባ ቤቶች አስተዳደር ጋር የኪራይ ውል እንዲዋዋሉ ተጠይቀው የነበር ነገር ግን አሁን የእነሱ ብቻ ተመርጦ ካርታ ለማሠራት በሂደት ላይ የሚገኙ ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በርካታ ሰነዶች ለአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል አቅርበዋል ።

ይህን ተከትሎ «እነኝህ ሰዎች እና እኛ በንጉሡ ዘመን መሬቱን የያዝንበት አግባብ አንድ ሆኖ ሳለ በምን ምክንያት እነሱ ሕጋዊ እውቅና አግኝተው የተቀረው አቤቱታ አቅራቢ ደግሞ እንዴት ሕጋዊ እውቅና ሳይሰጥ ቀረ?» ብለው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት መጠየቃቸውን ይገልጻሉ፡፡

ነገር ግን ጉዳዩ የሚመለከታቸው ከወረዳ እስከ ክፍለ ከተማ ያሉ አካላት ምንም አይነት ምላሽ ሊሰጡ ፈቃደኛ አለመሆቸውን አብራርተዋል። ምላሽ በማጣታቸውም እስካሁን ድረስ ከፍተኛ እንግልት ላይ መሆናቸውን አመላክተዋል።

በልዩነት ካርታ የተሰጣቸው ሰዎች እና የቅሬታ አቅራቢዎቹ የጂአይኤስ እና የሲአይ ኤስ መረጃ ምን ይመስላል? ተብለው በአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል የተጠየቁት አቤቱታ አቅራቢው፤ ሁላቸውም በንጉሡ ዘመን በተመሳሳይ ሁኔታ መሬቱን እንዳገኙት እና በ1988ቱም የአየር ካርታ ላይ እንደሚታዩ ማረጋገጫ ከክፍለ ከተማውም የኮፒ ግልባጭ እንደተሰጣቸው ይናገራሉ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ቤቶች ባለቤት አልባ መባሉ አግባብነት የለውም የሚሉት ቅሬታ አቅራቢው በቤቱ በየስማችን የቤት ቁጥር ፋይል ወጥቶልን በማንኛው ነገር ላይ የምንስተናገድ ሆኖ ሳለ ባለቤት አልባ ቤቶች መሰኘቱ በራሱ ትክክል አለመሆኑን አጽንኦት ሰጥተው ይናገራሉ፡፡

በድርጅቱ የተቀጠሩ ሰዎች በወቅቱ በየቤታቸው የራሳቸው ውሃ እና መብራት እንዳልበራቸው ነገር ግን ከሰፈሩ አንድ በአቅም ሻል የሚል ሰው ካለ ለተቀሩት ሰፈር ሰዎች ውሀና መብራት በትውስት ይሰጥ እንደነበር ያስረዳሉ።ነገሮች እየዋሉ እያደሩ ሲመጡ ግን ሁሉም ሰው በስሙ መብራት እና ውሃ ማስገባቱን ይገልጻሉ።

ድርጅቱ ወደ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ከተላለፈ ጀምሮ ሁሉም የሰፈሩ ነዋሪዎች በየራሳቸው ውሃ እና መብራት ማስገባታቸውን ይገልጻሉ። ሁሉም ሰው የድርጅቱ ሠራተኛ ስለነበር ድርጅቱ ለሠራተኞቹ እንደ ትብብር ውሃ በአጥር ውስጥ እያሾለከ ይሰጥ ነበር። ከሠራተኞች ደመወዝ የሚቆረጥ የመብራት ክፍያም የሚከፍለው ድርጅቱ እንደነበር ያስረዳሉ።

ለሠራተኞቹ የመብራት ክፍያ መክፈል እና ሠራተኞቹ ውሃ ባልነበራቸው ጊዜ በአጥር አሾልከው ውሃ መቅዳታቸው ደግሞ ውዝግብ ያስነሱት ቤቶች የፋብሪካው ናቸው ሊያስብ የሚችል መሠረት እንደሌለው እና የሠራተኞችንም የቤት ባለቤትነት መብት የሚያሳጣ እንዳልሆነ ያስረዳሉ፡፡

እስከዛሬ ድረስ ጉዳዩን ሰምቶ እና አጣርቶ መልስ የሰጠን አንድም አካል የለም የሚሉት አቶ አሥራት ፤ በአንድ ግለሰብ ማንአለብኝነት በተጻፈ ደብዳቤ ይህ ሁሉ አባወራ ለበርካታ ዓመታት መሰቃየቱ በወረዳቸው ያለውን የመልካም አስተዳደር ችግር ሁነኛ ማሳያ መሆኑን ይገልጻሉ።

ሌላኛው አቤቱታ አቅራቢ አቶ ሳምሶን ይልማ ይባላሉ። በአዋሽ ቆዳ አካባቢ የቤት ቁጥር 146 ነዋሪ ናቸው። እንደ አቶ ሳምሶን ገለጻ ፤ ጉዳዩን እየተከታተሉ ለረጅም ጊዜያት ቆይተዋል። ይህ ችግራቸው እንዲፈታ ለበርካታ ዓመታት ያልገቡበት የመንግሥት ቢሮ የለም። ይሁንና በወረዳቸው ብሎም በክፍለ ከተማቸው ከፍተኛ የሆኑ አስተዳደር ችግሮች በመኖራቸው ሳቢያ የተፈጸመባቸው ግፍ የሚፈታው አካል አልተገኘም።

ይህ ጉዳይ ግልጽ እና የሚታይ ነገር ነው የሚሉት አቶ ሳምሶን ፤ ጉዳዩን እስከከንቲባ ጽሕፈት ቤት ድረስ እንደወሰዱት ይገልጻሉ።ይሁን እንጂ የከንቲባ ጽሕፈት ቤትም ጉዳዩን መልሶ ችግር ወደ ፈጠረው ወደታችው የአስተዳደር እርከን መመለሱን ያስረዳሉ፡፡

አሁን ላይ የቤታቸው ጣራ ቢፈርስ የቤቱን ጣራ ማስተካከል እንደማይችሉና መጸዳጃ ቤታቸውም ቢፈ ርስ ለማስገንባት ፈቃድ አናገኝም ያሉት አቶ ሳምሶን ፤ በመሆኑም የአካባቢው ማኅበረሰብ ለከፋ ችግር ተጋልጦ እንደሚገኝ አመላክተዋል።

እናት እና አባታቸው ከ60 ዓመት በላይ የኖሩበት ቤት በሰነድ አልባ ተመዝግቦ ካርታ የሚያገኙበት መብት ሊፈጠርላቸው ሲገባ የመንግሥት ሹመኞች በሚፈጥሩት አግባብ ያልሆነ ምክንያት ጉዳዩ እስከዛሬ ድረስ ሊፈታ አልቻለም። በዚህም የአካባቢው ነዋሪዎች ለከፋ ችግር ተጋልጠው እንደሚገኙ ይናገራሉ።

«እኛ ቤት ብትመጣ በቤቱ መኖር ከጀመርን አራተኛ ትውልድ ደርሷል» የሚሉት አቶ ሳምሶን ፤ መኖሪያ ቤታቸውም የጂአይሴ እና የሲኤ ኤስ ማስረጃዎችም በእጃቸው እንደሚገኙ አመላክተዋል። ይሁን እንጂ የአየር ካርታውን እና የሲአይ ኤስ መረጃ ለወረዳው እና ለክፍለ ከተማው ቢያሳዩም መልስ ሊሰጣቸው የቻለ አካል አለመኖሩን ይገልጻሉ።

እንደ አቶ ሳምሶን ገለጻ ፤ አሁን ላይ እየተንገላቱ ያሉት ሰዎች ከአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ሠራተኞች ውጭ በአካባቢው ሌላ ሰዎች መኖር ሳይጀምሩ የነበሩ የአካባቢው ነባር ሰዎች ናቸው። ከነባር ሰዎች በኋላ በሕገ ወጥ መንገድ መጥተው መሬት የያዙ ሰዎች በሰነድ አልባ ታቅፈው መብት ተፈጥሮላቸው ባለይዞታ ሲደረጉ ነባር ነዋሪዎቹ ግን መብታው ተነፍጎ እንዲሁ እየተሰቃዩ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

አሁን ላይ በራሳቸው ቤት እየደረሰባቸው ያለውን ግፍ ቀድመው ቢያውቁ ኖሮ በአካባቢው በጣም ብዙ ባዶ ቦታዎች ስለነበሩ ሌሎች እንዳደረጉት በሕገ ወጥ መንገድ ባዶ ቦታዎችን በመያዝ በሰነድ አልባ መብት ሊፈጠርላቸው እንደሚችል ያስረዳሉ። ይህ ሁሉ ችግር የተፈጠረው በአንድ ግለሰብ ውሳኔ በመሆኑ እየደረሰብን ያለውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ይወቅልን ሲሉ ተናግረዋል።

ከአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ አቻ የሆነው አቃቂ ጨርቃ ጨርቅ በፋብሪካው ዙሪያ በሚገኝ ቦታ ላይ ከ47/67 ዐዋጅ በፊት ለሠራተኞቹ መኖሪያ ሠርቶ ነበር። ሠራተኞችም ሲኖሩበት ነበር። ይህ ማለት ቤቶቹ የፋብሪካው ነበሩ። በመሆኑም መንግሥት በ47/67 አዋጅ ትርፍ ቤቶቹን ሲወርስ ለፋብሪካው ሠራተኞች መኖሪያ የተሠሩት ቤቶች ጭምር ተወረሱ። አሁንም ድርጅቱን ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ሲረከብ የተረከበው ፋብሪካውን ብቻ ሳይሆን ለፋብሪካው ለሠራተኞች የተሠሩ ቤቶች ጭምር ነው፡፡

የአዋሽ ፋብሪካ ሠራተኞች ቤቶች ግን በሠራተኞች በራሳቸው የገንዘብ እና ጉልበት ወጭ የተሠሩ ስለነበሩ በአዋጅ 47/67ም አልተወረሱም፤ ፋብሪካውን ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ሲረከብ ቤቶችን አልተ ረከበም። ምክንያቱም ቤቶቹ የግለሰቦቹ እንጂ የመን ግሥት ስላልሆኑ።

በወቅቱ የአዋሽ ፋብሪካ ቤቶች የነበሩ ሦስት ቤቶች ንብረትነታቸው ከፋብሪካው ስለነበሩ በአዋጅ 47/67 ድርጅቱ ሲወረስ ቤቶችም አብረው መወረሳቸውን ይገልጻሉ። የአዲስ ዘመን ጋዜጣም ይህንኑ በቦታው ተገኝቶ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

እነኝህ ሦስት ቤቶች በወቅቱ የመኖሪያ ቤቶች የነበሩ። ነገር ግን የፋብሪካው ንብረት ስለነበሩ በአዋጅ 47/67 ሊወረሱ ችለዋል የሚሉት አቶ ሳምሶን ፤ የ65ቱ አባወራ መኖሪያ ቤቶች የእውነት የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ቢሆኑ ኖሮ በወቅቱ የነበረውን መንግሥት ከመውረስ ማን እና ምን ይከለክለው ነበር? ሲሉ ይጠይቃሉ። ቤቶቹ በአዋጁ ያልተወሰዱትም የሠራተኞቹ ስለነበሩ መሆኑን ያስረዳሉ።

በወቅቱ ትርፍ ቤት የነበራቸው ነገር ግን የአዋሽ ቆዳ ሠራተኛ ሆነው በፋብሪካው ዙሪያ ቤት ሠርተው ይኖሩ የነበሩ በርካታ ሰዎች በሌላ ቦታ ይገኝ የነበረው ቤታቸው በ47/67 ዓዋጅ እንደተወረሱ ያስረዳሉ።

የአባወራዎቹ ቁጥር መጀመሪያ በነበሩት ሠራተኞች 65 ይባል እንጂ አሁን ላይ በቤቶቹ የሚገኙ ልጅ እና የልጅ ልጅ ጋር ተዳምሮ ከ250 በላይ አባወራዎች በሰፈሩ እየኖሩ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡

ሌላኛዋ አቤቱታ አቅራቢዋ ወይዘሮ ጥሩነሽ ወርቁ ይባላሉ። እንደ ወይዘሮ ጥሩነሽ ገለጻ ፤ አሁን ላይ ውዝግብ በተነሳበት ቦታ ላይ ከአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ መኖር እንደጀመሩ እና አራት ያህል መንግሥታት ሲፈራረቁም እርሳቸው በዚሁ ቤት እንደነበሩ ያስረዳሉ።

የወረዳ እና ክፍለ ከተማ አካላት ቤቱ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ነበር ይላሉ። ቤቶቹም በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ባለቤትነት የተሠሩ መሆናቸውን ይናገራሉ። እዚህ ላይ የእርስዎ እይታ ምንድን ነው? ስንል ጠይቀናቸው ነበር። ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ የሰጡት ወይዘሮ ጥሩነሽ ባለቤታቸው በአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ተቀጥረው ይሠሩ እንደነበር ገልጸው ፤ የባለቤታቸው ሥራ ሌሊት ሌሊት ስለነበር ለሥራቸው ቅርበት እና ለችግር እንዳይጋለጡ በመስጋት አሁን የሚኖሩበትን ቦታ ከአቶ ተሰማ ወልደማሪያም ገዝተው ቤት እንደሠሩበት ይጠቅሳሉ።

በገዙት ቦታ ላይ ቤት ለመሥራት አቅም ባጠራቸው ጊዜ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ በብድር ቤት ሠራላቸው። ይህ የሆነው ለበርካታ ሠራተኞች መሆኑ ይናገራሉ። ሠራተኛውም ቤቶቹን ድርጅቱ በብድር ሠርቶላቸው ስለነበር ድርጅቱ የከፈለላቸውን ገንዘብ በየወሩ ከደመዛቸው እየተቆረጠ ለድርጅቱ ገቢ ይደረግ ነበር። ድርጅቱ የከፈላቸውን ገንዘብ ከወር ደመወዛቸው ከፍለው ሲጨርሱ ቤቱን የራሳቸው ማድረጋቸውን ይናገራሉ፡፡

ነገር ግን አንዱ ሲሾም አንዱ ሲሻር የቤታቸውን ጉዳይ አንዱም ሳይፈጽምላቸው እዚህ መድረሳቸውን ይገልጻሉ።

ሌላው አቤቱታ አቅራቢ የ84 አመት አዛውንቱ አቶ አሰፋ አላብሴ ናቸው። እንደ አቶ አሰፋ ገለጻ ፤ በዚህ ቤት መኖር የጀመሩት በ1950ዎቹ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ሲመሠረት ጀምሮ ነው። በዚህ ቤትም ከ60 ዓመታት በላይ ኖረዋል። አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ሲቀጠሩ ወርሐዊ ደመወዛቸው 75 ሳንቲም ነበር። አሁን ላይ በጡረታ የሚገኙ ሲሆን ወርሐዊ የጡረታ ገንዘባቸውም 95 ብር ደርሷል። አሁን ውዝግብ በተነሳበት ቤት 10 ልጆች እና ሰባት የልጅ ልጆች አሳድገው ለወግ ለማዕረግ አድርሰዋል።

አቶ አሰፋ አላብሴን ቤቱን ማን እንደሠራው ያውቃሉ? የወረዳ እና የክፍለ ከተማ አካላት ቤቱን የሠራው አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ እንደሆነ ይናገራሉ። እዚህ ላይ የእርስዎ ሃሳብ ምንድን ነው ? ስንል ጠይቀናቸው ነበር። ለተጠየቁት ጥያቄ ምላሽ የሰጡት አቶ አሰፋ እንዳሉት ፤ሌሎች ቤቶች እንደኔ ፋብሪካው ሲመሠረት በነበሩ ባዶ ቦታዎች ላይ ሠራተኛው በራሱ ገንዘብ እና ጉልበት የሠራቸው ናቸው። ቤቶቹ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ቢሆኑማ ኖሮ በአዋጅ 47/67 ይወረሱ ነበር።ነገር ግን ቤቶቹ የሠራተኛው ስለነበሩ በአዋጁም አልተወረሱም።

ውሃ እና መብራት ጋር ተያይዞ ለበርካታ ዓመታት ከፋብሪካው ይጠቀሙ እንደነበር ያስታውሳሉ። ለመብራት እና ለውሃ የሚከፈለው ክፍያ ደግሞ ከደመ ወዛቸው የሚቆረጥ መሆኑን ጠቁመዋል። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መብራቱ እና ውሃው ለግለሰብ ቤት ሳይሆን ለፋብሪካው ማምረቻ ነው በመባሉ ከፋብሪካው ስበው ይጠቀሙበት የነበረው መብራት እና ውሃ ተቆረጠ። በዚህም ምክንያት መብራት እና ውሃ በማጣታቸው መብራት እና ውሃ ይሰጠን ሲሉ ለቀበሌ አመለከቱ። የሰፈሩን ችግር የተረዳውም ቀበሌ በሠራተኞች ወጭ ፤ በስማቸው መብራት እና ውሃ ተሰጣቸው።

ሌላኛዋ አቤቱታ አቅራቢ ወይዘሮ ወይንሸት ለማ ይባላሉ። እኝህ ግለሰብ የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ሲመሠረት የፋብሪካው ባለቤቶች በቦታው ፋብሪካውን ለማቋቋም በፈለጉ ጊዜ ፋብሪካው የተሠራበትን ቦታ የሸጡት አባወራ የአቶ ተሰማ ወልደማሪያም እና የወይዘሮ ይፍቱ ስራ አብዩ የልጅ ልጅ ናቸው።

እንደ ወይዘሮ ወይንሸት ገለጻ ፤ የአባታቸውን ስም የማታስታውሰው ነገርግን በልጅነት ልቦናቸው ስማቸውን ያረሷቸው «ካችክ» እና «ማንድሮስ» የተባሉ አርመናውያን የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካን ባለቤቶች ፋብሪካውን ለመገንባት ባዶ ቦታ ከእርሳቸው ቤተሰቦች እንደገዙ ያስታውሳሉ። ቦታው የተሸጠውም ሃያ ብር በማይሞላ ገንዘብ ነው። ያንንም ገንዘብ ለአርመናውያኑ አጠናቀው እንዳልከፈሉ ይናገራሉ።

የአዋሽ ቆዳ ፋብሪካ ሠራተኞች በፋብሪካው ዙሪያ ሲሰፍሩ የተወሰኑት ሠራተኞች ከእርሳቸው ቤተሰቦች በትንሽ ብር ቦታ ገዝተው ቤት የሠሩ ሲሆን አብዛኛዎቹ ሠራተኞች ግን ከቤተሰቦቻቸው በነጻ መሬት ተሰጥቷቸው ቤት የሠሩ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

አሁን ላይ የወረዳ 6 ቤቶች አስተዳደር «ቤቶች የኔ ናቸው ማለቱ ከእውነት የራቀ» ነው ሲሉ ይናገራሉ፡፡

ውድ አንባቢያን በክፍል ሁለት ዝግጅታችን ከሰነዶች የተገኙ ማስረጃዎችን ፤ ጉዳዩ የሚመ ለከታቸውን የወረዳ እና የክፍለ ከተማ አመራሮች ምላሽ እንዲሁም የጋዜጠኛውን ትዝብት ይዘን የምንቀርብ ይሆናል። እስከዚያው ቸር እንሰንብት ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው።የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል።ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል።በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "የሹመት ደብዳቤና ይዘቱ"

## የመነሻ ሀሳብ

ከሀገራዊ ብሂሎቻችን መካከል ስለ ሹመትና ሹም የሚናገሩት አባባሎች በርከት ያለ ቁጥር እንዳላቸው በሚገባ የተረዳሁት በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ ዝግጅት ሳደርግ ነበር። "ሹመት ላወቀው ይከብደዋል፤ ላላወቀበት ደግሞ ያሳብደዋል" የሚለው አንዱ ዘለላ አባባል ፈገግ ያስደረገኝን ያህል "ሹምና ጥጥ እያደር ይከብዳል" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገርም "እውነትም!" አሰኝቶ ውስጤን እንዳነዘረኝ መደበቅ አልሻም።

ሹመት ከጥጥ ጋር ተነጻጽሮ ይከብዳል መባሉ፤ ውሎ ሲያድር የሹሙ አመራርም እንዲሁ "ውሃ እንደነካው ጥጥ" እየከበደና የተመሪውን ጫንቃ ቁልቁል እየተጫነ ለምሬት እንደሚዳርግ ለመግለጽ ነው። ይህንን የመንደርደሪያ አንቀጽ ለመነሻ እንዲያግዝ ካስታወስን ዘንድ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ ምክንያት ወደ ሆነኝ የግል ገጠመኝ ልሸጋገር።

እ.ኤ.አ ......በአሜሪካዋ የሐዋይ ክፍለ ግዛት በተለይም በፓስፊክ ውቅያኖስ መካከል ከሚገኙት ውብ ደሴቶች መካከል ማዊ በመባል በምትታወቀው በአንደኛዋ ደሴት እምብርት ላይ በሚገኝ አንድ ዓለም አቀፍ የሥልጠና ማዕከል ለመገኘት ዕድል አጋጥሞኝ ነበር። የሥልጠናው ዋና ትኩረት በዋነኛነት በከፍተኛ የአመራር ጥበብና በኮሙዩኒኬሽን የዕውቀት ዘርፎች ላይ ያተኮረ ሲሆን የሥልጠናው ተሳታፊዎችም ከሃያ ሰባት ያህል ሀገራት የተውጣጡና በተለያዩ ደረጃዎች ሀገራቸውን የሚያገለግሉ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ነበሩ።

ትምህርቱን ይሰጡ የነበሩት መምህራንም እንዲሁ በየተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በርካታ መጽሐፍትን የጻፉ፣ በተለያዩ የዓለማችን ዩኒቨርስቲዎች የሚያስተምሩና አንቱታን ያተረፉ ታላላቅ ምሑራን ነበሩ። እነዚያን ከመሳሰሉ "የቀለም ቀንድ" ሊቃውንት ዕውቀታቸውንና የግላቸውን ተሞክሮ መቅሰም በግል እድለኝነት ቢመስልም ሰፋ ተደርጎ ሲታሰብ ግን "ወይ ሀገሬ!" አሰኝቶ ቁጭት ላይ የሚጥሉ ብዙ ትምህርቶችን ለመማር ችያለሁ።

ጸሐፊው ሥልጠናውን አጠናቆ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላም "የአመራር ጥበብ" በሚል ርዕስ ተደጋግሞ ለሕትመት የበቃች አንዲት መለስተኛ መጽሐፍ ለንባብ ለማብቃት ሞክሯል። ለመጽሐፏ መታተም ሁለት ዋና ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። አንድም፡- ጸሐፊው ያገኘውን እውቀት "የጋን ውስጥ መብራት" አድርጎ ለራሱ ብቻ ከማስቀረት ይልቅ ለወገኖቹ የማካፈል ጉጉት ስለነበረው፤ ሁለትም፡- በሥልጠናው ማጠቃለያ ላይ እያንዳንዱ ሠልጣኝ ያገኘውን እውቀት የሀገሩን ዐውድ በሚመጥን አቀራረብ ሌሎችን እንዲያሰለጥንና የተማረውን እንዲያካፍል "የቃል ኪዳን ያህል" አደራ ገብቶ ስለነበርም ነው።

እጅግ የተከበረና ጠቃሚ እውቀት የገበየንበትን ያንን ዓለም አቀፍ ሥልጠና በተያዘለት መርሐ ግብር መሠረት እንዲተገበር ለማስተባበር የተመረጡት ታላቁ ኢትዮጵያዊ ጄኔራል ታዬ ጥላሁን ነበሩ። ብርጋዴዮር ጄኔራል ታዬ ጥላሁን ዕድሉን አግኝተው ምርጫውን ያሸነፉት ሀገራቸውን ባገለገሉበት ዘመን ባተረፉት መልካም ዝናና አክብሮት ይሁንታ በማግኘታቸው ነበር። ጄኔራል ታዬ ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት እስከ ወታደራዊው የደርግ አገዛዝ ዘመን ድረስ በአየር ኃይልና በባሕር ኃይል ተቋማት ውስጥ በከፍተኛ እርከን አገልግለዋል።

በመቀጥልም በሀገር አስተዳደርና በመከላከያ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ውስጥ በሚኒስትርነት ማዕረግ ከፍተኛ የአገልግሎት ወንበር ላይ የተቀመጡ ሲሆን በመጨረሻም በውጭ ሀገራት አምባሳደርነት በሚያገለግሉበት ወቅት የወታደራዊው ደርግ አገዛዝ ስላላስደሰታቸው ሥልጣናቸውን በመተው ስደትን መርጠው በአሜሪካ ይኖሩ ነበር። የሥልጠና ማዕከሉ ኃላፊዎች "በሙብራት አፈላልገው" የማስተባበሩን ኃላፊነት የሰጧቸው በአገ ልግሎታቸውና በተሞክሯቸው ግዝፈት ተማርከው እንደሆነ ለመገመት አይከብድም።

ዓለም ባከበራቸውና ይህ ጸሐፊም በርቀት ሲያከብራቸው የኖረው እኚህ ታላቅ ሰብዕና የተላበሱ ኢትዮጵያዊ በሚያስተባብሩት ሥልጠና ላይ መገኘት ማለት ግጥምጥሞሽ ተብሎ የሚታለፍ ብቻ ሳይሆን መባረክም ጭምር እንደሆነ በጽኑ ያምናል። ከጄኔራሉ ጋር ስለ ሀገር ጉዳይ ስንወያይ ያነሳናቸውን እጅግ ጠቃሚ ነጥቦች በተመለከተ ጊዜው ሲፈቅድ በዝርዝር ለማካፈል እሞክራለሁ። ስለ ጄኔራል ታዬ ጥላሁን ይበልጥ ለማወቅ ካስፈለገ፤ "የሕይወቴ ጉዞ" በሚል ርዕስ በወንድዬ ዓሊ አሰናጅነት በ2010 ዓ.ም የታተመውን ግለ ታሪክ መጽሐፋቸውን ማንበብ ይቻላል።

### የዐይን ከፋቹ ሥልጠና ትሩፋት፤

ከላይ በተጠቀሰው የሥልጠና መርሐ ግብርና በተለይም በቡድን ውይይቶች መካከል ተነስተው ከነበሩ በርካታ ሃሳቦች መካከል ከዛሬው ርዕሰ ጉዳያችን ጋር የሚጎዳኙትን አንዳንድ ነጥቦች ልጠቃቅስ። "የየሀገራችሁ መንግሥታት በከፍተኛ የሥልጣን እርከን ላይ ለሚሾሟቸው ባለስልጣናት የሚሰጧው የሹመት ደብዳቤዎች ይዘት ምን ይመስላል?" በኮሙዩኒኬሽን አሠልጣኞችን አማካይነት ለቡድን ውይይት ከተሰጡን ጥያቄዎች መካከል አንዱ ነበር። ይገርማል! ይህ አነስተኛ የሚመስል ርዕሰ ጉዳይ ለካንስ ብዙ የሚተነተኑ ሃሳቦችን የያዘ ኖሯል።

እውነቱን ለመመስከር ከዚያ ዕለት በፊት አንድም ቀን ስለ ሹመት ደብዳቤዎች የይዘት ምንነት አስቤ አላውቅም ነበር። በቡድን ውይይቱም ላይ እንደ ሌሎች ተሳታፊዎች ንቁ ነበርኩ ለማለት አይቻልም። በተለይም በአፍሪካ ወንድሞቻችን ይሰጡ የነበሩት በሳል አስተያየቶች ይህንን ጸሐፊ ብቻ ሳይሆን ከአፍሪካ ውጭ የመጡ የሌሎች ሀገራትን ተሳታፊያን ጭምር ማስደመሙ አልቀረም።

ከናይጄሪያ የመጣው አንዱ ሠልጣኝ የሰጠው ሃሳብ ረዥም ሰዓታት አወያይቶን እንደነበርም አስታውሳለሁ። እንዲህ ነበር ያለው፡- "በአፍሪካውያን የሹመት ደብዳቤዎች ውስጥ ‹የተመደበልዎትን ጥቅማ ጥቅም እያገኙ› የሚል ሐረግ ካልታከለበት በስተቀር የሚሾሙት ግለሰቦች ደስተኛ ላይሆኑ ይችላሉ። ለሹመት የቀረቡ ዕጩዎችም በደብዳቤያቸው ውስጥ ፈጥነው ለማንበብ የሚጣደፉት "ጥቅማ ጥቅም" አመልካቿ ሀረግ በደማቁ መጻፏን እንጂ ለዝርዝር የሥራ መመሪያቸው ደንታ ያላቸው አይመስልም። እንዲያውም እጅግ የሚያስገርመው ነገር ከብዙ የሹመት ደብዳቤዎች ጋር ዝርዝር የሥራ መመሪያ መስጠት የተለመደ አይደለም። ምናልባትም መመሪያው በአለቃቸው ቢሮ በኩል በቃል ተነግሯቸው ይሆናል ወይንም ‹ዋኝታችሁ ተወጡት› ተብሎም ሊሆን ይችላል"

ናይጄሪያዊው ሠልጣኝ ጓደኛችን ሃሳቡን በአጭሩ ለመቋጨት የፈለገ አይመስልም፡- "የአፍሪካ መሪዎች ለሚሾሟቸው ባለሥልጣናት የሚጽፉት የሹመት ደብዳቤ ርዝመት በአንድ ዐረፍተ ነገር የተጠቃለለ መሆኑም እጅግ ያስገርማል። ‹ከዚህ ቀን ጀምሮ ጥቅማ ጥቅምዎ ተከብሮ የ....... ሚኒስትር/ኃላፊ/ኮሚሽነር... ሆነው የተሾሙ መሆንዎን አስታውቃለሁ። ይኼው ነው።"

ከዚህ አስተያየት በኋላ ውይይቱ ተጋግሎ በመቀጠል እያንዳንዱ ሠልጣኝ የየሀገሩን ተሞክሮ እየተሽቀዳደመ ይተርክ ጀመር። "በእኔ ሀገር..." አለ አንዱ የእስያ ሀገር ሠልጣኝ፡- "ማንም የመንግሥት ሹመኛ ሥልጣን በተሰጠው ዕለት በቀጥታ በሚተላለፍ የሚዲያ መርሐ ግብር ስለተሾመበት የኃላፊነት ቦታ ምን ራዕይ ኖሮት ምን ለማስፈጸም እንዲሚተጋ ለሕዝቡ በይፋ ያስታውቃል። ከሚዲያ ባለሙያዎች ለሚቀርቡለት ዝርዝር ጥያቄዎችም ተገቢውን መልስና ማብራሪያ የመስጠት ግዴታ አለበት። ቃል የገባውን ውጤት ማሳካት ካልቻለም ኃላፊነቱን በፈቃዱ እንደሚለቅ በግልጽ ያስታውቃል።"

ይህ እስያዊ ሠልጣኝ ከልቡ ይህንን አስተያየት ሲሰጥ ከአፍሪካ ሀገራት የተጋበዝነው ተሳታፊዎች "ወይ ነዶ! አይ እምዬ አፍሪካ!" በሚል ዓይነት ቁጭት እየተጠቃቀስን እርስ በእርስ መተያየታችንን አስታውሳለሁ። ምክንያቱም የእኛይቱ አፍሪካ ለዚህን መሰሉ ግልጸኝነት ስላልታደለች ወይንም መሪዎቻችን ስላላደሉን መሆኑን ልብ ይሏል።

### "ኢትዮጵያ ሆይ! ተጠየቂ!?"

ይህ ጸሐፊ ከዚያ ሥልጠና በኋላ የበርካታ የሹመት ደብዳቤዎችን ናሙና ለመመልከት ሞክሯል። መነሻ ያደረገውም የዳግማዊ አጤ ምኒልክን ዘመን ነው። በደብዳቤ አጻጻፍ ወግና ሥርዓት ይህ የምኒልክ ዘመን የተለየ ባህርይ አለው። በአጠቃላይ ሲፈተሽ ንጉሠ ነገሥቱ በጻፏቸው አብዛኞቹ የሹመት ደብዳቤዎች ውስጥ የተጠቀሱት ቃላት ትሕትና የሚስተዋልባቸው፣ በርህራሄ የታጀቡና እንደ ሀገር መሪ ሳይሆን በአንድ ደረጃ ላይ የሚገኝ የሥራ ባልደረባ የሚጽፈውን ዓይነት ይዘት ያላቸው ናቸው።

አጤ ምኒልክ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት የተጻጻፏቸውንና በጳውሎስ ኞኞ አማካይነት የተሰባሰቡትን ዳጎስ ያሉ ባለሁለት ጥራዝ መጽሐፍት የአርትኦቱን ሥራ የሠራው ይህ ጸሐፊ ስለሆነ የደብዳቤ ባሕርያቱን በሚገባ ለመረዳት እድል አጋጥሞታል። ዘርዘር በሚሉት የሹመት ደብዳቤዎቹ ማጠቃለያ ላይ ባለስልጣናቱ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ጭምር ጠበቅ ያለ የአደራ ቃል ይጠቀሙ ነበር።

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመንም ቢሆን በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካይነት ይጻፉ የነበሩት የሹመት ደብዳቤዎች የአደራ ቃሉ ጠንከር ይል ካልሆነ በስተቀር "የጥቅማ ጥቅም" ጉዳይ የተገለጸባቸውን ደብዳቤዎች በግሌ ፈልጌ ለማንበብ አልቻልኩም። ንጉሡ ሹመት ከሰጡም በኋላ ሳይውል ሳያድር የተሾሙት ባለሥልጣናት ቤተ መንግሥት እየተጠሩ የአደራውን ቃል ያጠናክሩ እንደነበር ከክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም ግለ ታሪክ መጽሐፍ ላይ ተጠቅሶ አንብቤያለሁ።

"በግርማዊነታቸው መልካም ፈቃድና ትዕዛዝ የትምህርትና ሥነ ጥበብ ዋና ዳሬክተር መሆኔን ጸሐፌ ትዕዛዙ ነገሩኝና ንጉሡ ነገሥቱን እጅ ነስተን ወደየቤታችን ተመለስን። ከጥቂት ቀናት በኋላ ከጃንሆይ ፊት ለጉዳይ ቀረብሁና "የተሰጠህ ትልቅ ሥራ ነው አሉ።" እኔም "አዎን ጃንሆይ! ካሁኑ ከባድነቱ እየተሰማኝ ነው" አልኋቸውና በፈገግታ ተለያየን" (የሕይወቴ ትዝታ - ገጽ 43)።

የዘመነ ደርጉ ሥርዓት ብዙ ያነጋግራል፤ ያወያያልም። ርግጠኛ መሆን የሚቻለው ግን "አብዮቱን በመስዋዕትነት ጭምር ከግብ እንድታደርሱ" ከሚል መመሪያ በዘለለ "ተገቢው ጥቅማ ጥቅም ተጠብቅዎሎት..." የሚል ሐረግ እድል ገጥሞኝ ለማየት በቻልኳቸው የሹመት ደብዳቤዎች ውስጥ ለማንበብ አልቻልኩም። ምንም እንኳን ተጨማሪ ጥናት የሚጠይቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ይሄ "የጥቅማ ጥቅም አጽንኦት" ጉዳይ በሹመት ደብዳቤዎች ላይ መጠቀስ የጀመረው ከዘመነ ሕወሓት/ ኢሕአዴግ ዘመን ጀምሮ ይሆንን የሚል ጥርጣሬ አድሮብኛል። ወደፊት ጊዜው ሲፈቅድ ጠለቅ ያለ ጥናት ማድረግ እንደሚገባኝ ተረድቻለሁ።

በዚህ ጽሑፍ ለማንሳት ወደ ተንደረደርኩባቸው አንዳንድ ጥያቄዎች ልመለስ። ማንኛውም የኃላፊነት ወንበር የራሱ የሆነና ሹመቱን የሚመጥን በዝርዝር የተወሰነ ጥቅማ ጥቅም እንዳለው ይታወቃል። ይህ አሠራር አዲስ ሳይሆን በየትኞቹም ሀገራት ሥርዓተ መንግሥታት ውስጥ የነበረና ዛሬም እየተተገበረ ያለ ደንብ ነው። ከሁለትም ሦስት መኪና፣ የሚያዝናና መኖሪያ ቤት፣ ልዩ ጥበቃና እጀባ ወዘተ. እንደ ሥልጣናቸው ክብደትና ቅለት መሰጠቱ የተለመደና የታወቀ ነው።

እውነታው ይህ ሆኖ እያለ በየሹመት ደብዳቤዎቹ ውስጥ ለታወቀ ባህልና ልማድ "የጥቅማ ጥቅም ጉዳይ" ከአገልግሎት አደራ ቀድሞ ለመጠቀስ ስለምን ያስፈልጋል? በዚህ ጸሐፊ መረዳት "የአዋጁን በጓዳ" እንዲሉ "ፀሐይ የምትወጣው በምሥራቅ በኩል ነው" የሚለውን ተፈጥሯዊ እውነታ ካልተረዳችሁ የማለት ያህል ያስገምታል። ለነገሩስ የጥቅማ ጥቅሙ ጉዳይ በደብዳቤው ውስጥ ባይገለጽስ ሊቀር የሚችል ጉዳይ ነው?

ደግ ደጉን እንመኝና እንደ እስያው ሠልጣኝ ጓደኛችን ገለጻ አንድ ባለ ሥልጣን በሀገራችን ከተሾመ በኋላ ከብዙኃን መገናኛ ባልደረቦችና አስፈላጊ ከሆነም እርሱ/እርሷ በተሾሙበት ዘርፍ ከሰለጠኑ ባለሙያዎችና ዜጎች ተሹዋሚው ለማሳካት ስለሚያቅደው/ስለምታቅደው የሥራ ፕሮግራም ከዜጎች ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎችና አስተያየቶች መድረክ ተመቻችቶ ውይይት ማድረግ ቢቻል ለሀገር እድገት አይበጅም? መቼም "እኛ ዜጎች እንደምናምነው፤ ባለስልጣኖቻችንም አሌ ሊሉ እንደማችሉት" የምርጫ ካርዳችንን ተጠቅመን "እንደራሴያችን" እንዲሆኑ ለወንበራቸው ክብር ያበቃናቸው እንዲያገለግሉን እንጂ ለራሳቸው "እንደ ራሳቸው" ሆነው ጥቅማ ጥቅም ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ አይደለም።

እንደ ድፍረት ካልተቆጠረብን በስተቀር በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እያስተዋልናቸው ያሉትን ሀገራዊ ቀውሶችና ተግዳሮቶች ማርገብና በጥበብ ማስከን የተሳናቸው አንዳንድ የመንግሥት ሹመኞች "የተሰጠኝን ኃላፊነት መወጣት ስላልቻልኩ ኃላፊነቴን በፈቃዴ ለቅቄያለሁ" ሲሉ ማድመጥ የምንመኘው ብቻ ሳይሆን ሆኖ ብናየው በእጅጉ እንደምንናፍቅ ለሚመለከታቸው መሪዎቻችን ይድረስ ብንል ያስወቅሰን ይሆን? አይመስለኝም።

"ሹመት ናፋቂ ውሎው ወንዝ ዳር ነው" ይባላል፤ ለምን ቢሉ፡- "የውኃውና የድንጋዩ ቻቻታ የሕዝብ አቤቱታ ይመስለዋል" እንዲሉ ካልሆነ በስተቀር "ሹመት ሺህ ሞት ነው" በማለት እንደ ብሂሉ ደፍረን ባንናገርም እንኳን፤ "ሕዝብን ማገልገል ከጥቅማ ጥቅም በላይ የሆነ ምድራዊና ሰማያዊ አደራ" መሆኑን ባለሥልጣኖቻችን በተግባራቸው ቢያረጋግጡልን እያከበርናቸው እንመራላቸዋለን። "ከግላዊ ጥቅማ ጥቅሙ ባሻገር ምን ያህሉ ሹም ሕዝብን ለማገልገል ራሱን ለሕዝብ ጥቅም አድርጎ እንደሚሰጥ" ቢፈተሽ ብዙ ገመና ይገለጥ ነበር።

"ጥቅማ ጥቅሙ ብቻ እያማለላቸው" ፍሬያቸው ሲጎመዝዝና አደራ በል ሆነው ስናስተውል በየጓዳችን ከማማትና ከመታዘብ አልፈን ተርፈን እንደየሃይማኖታችን በየቤተ እምነቶቻችን ታዛ ሥር ስንሰባሰብ በፈጣሪ ፊት ምን ብለን እንደምንጸልይባቸው ይጠፋቸዋል ማለት አይቻልም። ከአሁን ቀደም ባስነበብኩት ጽሑፌ ውስጥ የጠቀስኩትን አንድ አባባል አስታውሼ ርዕሰ ጉዳዬን ልደምድም። "ሹመኞቹ የሀገሬ የሕዝብ ባላደራዎች ሆይ! እንደምትኖሩ ሆናችሁ ሥሩ፤ እንደምትሞቱ ሆናችሁ ኑሩ!"። ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

ኢኮኖሚ

## ንግድና ግብይት

# የገበያ ማረጋጋቱ ሌላ አማራጭ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን በመሠረታዊነት በሀገር ውስጥ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች የምግብ ፍጆታ አቅርቦትን ማሟላት አንዱና ዋነኛው ተግባሩ ነው። ከዚህም ባለፈ በሀገር ውስጥ የሚታየውን የዋጋ ንረት የማረጋጋትና የስርጭት መጠን ክፍተትን የማስተካከል ኃላፊነት አለው። ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር በርካታ ኃላፊነቶች ያሉበት ቢሆንም ባለፉት በርካታ ዓመታት አገልግሎቱን በሚፈለገው ልክ መስጠት የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶች የተሟሉለት እንዳልሆነ መረጃዎች ያሳያሉ።

ኮርፖሬሽኑ በአራት የሥራ ዘርፎች ማለትም በእህልና ቡና ንግድ ሥራዎች፣ በኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ፣ በኢትዮጵያ የፍጆታ ንግድ ሥራ እና የግዢና ማማከር ተቋማትን በማዋሐድ እየሠራ ያለ ተቋም ሲሆን በተለይም በእህልና ቡና ንግድ ከ70 ዓመታት በላይ የአገልግሎት ልምድ አለው። በአትክልትና ፍራፍሬ ንግድም ከ40 ዓመታት በላይ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል።


ይሁን እንጂ ኮርፖሬሽኑ በአራቱም የንግድ ዘርፎች ሲሠራ በቆየባቸው በርካታ ዓመታት ለኪሳራ ተዳርጎ እንደነበር ከተቋሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ኮርፖሬሽኑ ከኪሳራ በመውጣት ውጤታማ ሥራ እየሠራ እንደሆነ ነው ይሄው መረጃ የጠቆመው። ኮርፖሬሽኑ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደመሆኑ ለማኅበረሰቡ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች መሠረታዊ የምግብ ፍጆታ አቅርቦት ማሟላትና በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ ማድረግ ዋነኛ ተግባሩ ነው።

በተለይም ሕዝብ በስፋት በሚኖርባቸው ትላልቅ ከተሞች ላይ የአቅርቦት እጥረትና የዋጋ ንረት ሲፈጠር ግንባር ቀደም ሚናን መጫወት ከኮርፖሬሽኑ ይጠበቃል። በቀጣይም በሀገሪቱ በየጊዜው የሚስተዋለውን የዋጋ ንረት ከመከላከል ጀምሮ ገበያን በማረጋጋት የተለያዩ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ ከኮርፖሬሽኑ የሚጠበቅ እንደሆነ ይታመናል።

በመሆኑም ኮርፖሬሽኑ በአሁኑ ወቅት ከአምራቹ እስከ ተጠቃሚው ያለውን የአቅርቦትና የግብይት ሰንሰለት ጤናማና ውጤታማ በማድረግ፤ ጤንነቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ለተጠቃሚው ተደራሽ ማድረግ የሚያስችለውን ሥራ አጠናክሮ ለመቀጠል በዝግጅት ላይ ይገኛል። ኮርፖሬሽኑ በሀገሪቱ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማና በዙሪያዋ ለሚገኙ የክልል ከተሞች ጭምር የተሻለ የምርት አቅርቦት ለማቅረብ ፈታኝ ሆኖበት የቆየውን ችግር የሚቀርፍለትን ዘመናዊና ባለዘርፈ ብዙ ቅይጥ አገልግሎት የሚሰጥ ሕንጻ አስገንብቶ ለመጠቀም አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ እያከናወነ ይገኛል።

የኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አቻ ደምሴ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳሉት፤ የኮርፖሬሽኑ ዓላማ ለማኅበረሰቡ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች መሠረታዊ የምግብ ፍጆታ አቅርቦት ማሟላት ነው። ይህም ሲባል አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ የእህልና የጥራጥሬ ምርቶችን ያቀርባል። በአገሪቱ ምርት በስፋት ከሚመረትባቸው አካባቢዎች ያለውን ምርት ገዝቶ፣ አከማችቶና አደራጅቶ እጥረት ወዳለባቸውና ሌሎች ተጠቃሚዎች ወደሚገኙበት አካባቢ ተደራሽ በማድረግ ኅብረተሰቡ ምርቱን በተመጣጣኝ ዋጋ ገዝቶ መጠቀም እንዲችል የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን ማሟላት ወሳኝ ነው።

ከሰሞኑም ኮርፖሬሽኑ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በተለምዶ የሺ ቶታል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ባለ 10 ወለል ቅይጥ አገልግሎት የሚሰጥ ሕንጻ ግንባታ



አቶ አቻ ደምሴ የኮርፖሬሽንዋና ስራ አስፈፃሚ

ሥራ ማስጀመሩም ለዚሁ ነው። ባለማቀዝቀዣ የቅይጥ ሕንጻ ግንባታው በተለይም የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ደረጃቸውን በጠበቀ መንገድ ሳይበላሹ ለረጅም ጊዜ ማቆየት የሚያስችል ሲሆን፤ ከዚህም ባለፈ ኮርፖሬሽኑ ከአምራቹ የሚቀበለውን የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ያለብልሽት ጥራቱን ጠብቆ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚያስችል ነው።

በአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ በዓመት ውስጥ በተወሰኑ ወራት ብቻ ምርት የሚገኝ በመሆኑ፣ ከምርት ወቅት በኋላ የምርት እጥረት በሚከሰትባቸው ወራት ኮርፖሬሽኑ ምርት አከማችቶ የሚያቆይ ይሆናል። አከማችቶ ያቆየውን ምርትም አውጥቶ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ያደርጋል። በተለይም ሰፊ ቁጥር ያለው ሕዝብ ይኖራል ተብሎ በሚገመትባቸው ሰፋፊ ከተሞች ውስጥ የመንግሥት ሠራተኞችን ጨምሮ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የከተማዋ ነዋሪዎች ምርቶቹን በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል። ኮርፖሬሽኑ ከሚያቀርባቸው የምርት አይነቶች መካከልም አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ የዳቦ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ጥራጥሬና ሌሎችም ይገኙበታል።

ኮርፖሬሽኑ ለመንግሥት ሠራተኞችና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነዋሪዎች ከሚያቀርበው ምርት በተጨማሪ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች በመሄድ ለሚሠሩና ሀገራዊ ኃላፊነት ውስጥ ለሚገኙ ማለትም ለሀገር መከላከያ ሠራዊት፣ ለፌዴራል ፖሊስና ለመሳሰሉት በተመሳሳይ ለምግብ ሬሽን የሚውል ምርት እያቀረበ እንደሆነም አቶ አቻ ይገልፃሉ።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንደሚናገሩት፤ ኮርፖሬሽኑ፤ ከአዲስ አበባ ከተማ በረጅም ርቀት ላይ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች በግል፣ በማኅበርና በትላልቅ ኩባንያዎች ጭምር የሚመረተውን አትክልትና ፍራፍሬ እስከ 900 ኪሎ ሜትር ርቀት ተጉዞ ምርቶቹን በቀጥታ ከአምራቾች ገዝቶና አደራጅቶ ለገበያ ያቀርባል።

ይህም አምራቹን በማበረታታት፣ ምርቱ ገበያ እንዲያገኝና በተመጣጣኝ ዋጋ መሸጥ እንዲችል ያደርጋል። አምራቹ ካመረተ በኋላ ገዢ በማጣት ማምረት እንዳያቆም ተመጣጣኝ ዋጋ ለአምራቹ በመክፈል ምርቱን ይገዛዋል፤ በተመሳሳይ ደግሞ በከተሞች የሚገኘው ምርት ፈላጊ ምርቱን በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት እንዲችል አጓጉዞና አደራጅቶ በማቅረብ ማኅበረሰቡ ተመጣጣኝ ምግብ ማግኘት እንዲችል ያደርጋል።

‹‹የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በቀላሉ የሚበላሽ እንደመሆኑ ከተመረተበት አካባቢ ወደ ተጠቃሚው እስኪደርስ ባለው ምልልስ ተበላሽቶ የሚጣለው ምርት ይበልጣል›› የሚሉት አቶ አቻ፤ ይህም በሀገሪቱ ለረጅም ጊዜ የቆየና አሁንም ያልተፈታ መሠረታዊ ችግር እንደሆነ ያስረዳሉ። ችግሩን ለመፍታት ከትራንስፖርት ጀምሮ ማቀዝቀዣ ያላቸው ተሽከርካሪዎችና ሌሎች መሠረተ ልማቶችም ያስፈልጋሉ። ምርቶቹ ከተጓጓዙ በኋላም ማቆየት የሚያስችል ማቀዝቀዣና ማደራጃ መጋዘኖች አስፈላጊና ወሳኝ መሆናቸውን የጠቀሱት አቶ አቻ፤ ይህም ጤንነቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ምርት ተደራጅቶ ለተጠቃሚው እንዲደርስ የሚያስችል ነው ብለዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው ከአዲስ አበባ ረጅም ርቀት ተጓጉዘው የሚመጡት የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በቀላሉ ለብልሽት የሚጋለጡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ይህን ችግር ለመፍታት ዘመናዊ ባለማቀዝቀዣ የቅይጥ ሕንጻ ግንባታው ወሳኝ ሆኖ መገኘቱን ይናገራሉ። የገበያ ማዕከልና የቢሮ አገልግሎትን ጨምሮ የሚገነባው ይህ ግንባታ ለበርካታ ጊዜ ታቅዶ እንደነበር ያስታወሱት አቶ አቻ፤ ግንባታው ሲጠናቀቅም ኮርፖሬሽኑ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎችና በዙሪያው ለሚገኙ የክልል ከተሞች ምርቶቹን ያሰራጫል። ኮርፖሬሽኑ የሚያቀርባቸው የተለያዩ ምርቶችም ማኅበረሰቡ ትክክለኛ የጥራት ማረጋገጫዎችን ተረድቶ ሊገዛና ሊጠቀምበት የሚያስችለው ነው ብለዋል።

‹‹የሀገር ውስጥ ምርት ደረጃውን የጠበቀና የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ ያሟላ መሆን እንዲችል ባለማቀዝቀዣ የቅይጥ ሕንጻው አይነተኛ ሚና ይኖረዋል፤ በተለይም በኢትዮጵያ የንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ውስጥ ለሚገኘው የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ አበርክቶው የጎላ ነው›› ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ኮርፖሬሽኑ በአገር ውስጥ አትክልትና ፍራፍሬን የሚያመርቱ ኩባንያዎች፣ ግለሰቦችና ማኅበራት እንደ ብርቱካን አይነት ጥራታቸውን የጠበቁ ምርቶችን በማምረት ከሀገር ውስጥ ባለፈም ወደ ውጭ ገበያ ይቀርባል። ለአብነትም በተያዘው በጀት ዓመት 64 በመቶ ፍራፍሬዎችን ወደ ውጭ ገበያ መላክ የተቻለ ሲሆን በቀጣይም ይኸው ተግባር ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ከአትክልትና ፍራፍሬ በተጨማሪ ቡናና የቅባት እህሎች እንዲሁም ጥራጥሬዎች ወደ ውጭ ገበያ ስለመላካቸው የጠቀሱት አቶ አቻ፤ የአቅርቦት እጥረቱ ክፍተት ቢኖረውም ከዕቅዱ አንጻር ግን የተሻለ ክንውን ያለው መሆኑን አስረድተዋል።

እንደዋና ሥራ አስፈፃሚው ማብራሪያ፣ ኮርፖሬሽኑ ገበያ የማረጋጋት ሥራን የሚሠራ በመሆኑ በተለያየ ጊዜ የሚፈጠረውን የምርት አቅርቦት እጥረትና የዋጋ ግሽበትን ለማረጋጋት ኮርፖሬሽኑ አማራጭ ሆኖ ይቀርባል። በተለይም ለመንግሥት ሠራተኞችና ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች የተለያዩ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ገበያን በማረጋጋት ቀዳሚ ነው። ለአብነትም በአሁኑ ወቅት በጤፍ ምርት ላይ እየተስተዋለ ያለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት ጤፍ ገበያ ላይ በኩንታል ከስምንት ሺ ብር በላይ ሲሸጥ ኮርፖሬሽኑ አንድ ኩንታል ነጭ ጤፍ በ5,250 ብር ለአዲስ አበባና ለኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ሠራተኞች፣ ለተማሪዎች ምገባ፣ ለኅብረት ሥራ ዩኒየኖች፣ ለማረሚያ ቤቶች፣ ለፌደራልና ለኦሮሚያ ፖሊስ፣ እንዲሁም ለድሬዳዋ፣ ለባሕርዳርና ለደሴ ከተማ ነዋሪዎች በማቅረብ ገበያውን በማረጋጋት ሰፊ ሥራ እየሠራ ይገኛል።

ሲሚንቶ፣ ዘይትና ሌሎች ምርቶችንም በማቅረብ ገበያን የማረጋጋት ሥራ እየሠራ የሚገኘው ኮርፖሬሽኑ፤ በተለይም ፓልም የምግብ ዘይት ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በተሰጠው ኮታ መሠረት ለአዲስ አበባ፣ ለአማራ፣ ለሱማሌ፣ ለድሬዳዋ፣ ለሐረር፣ ለደቡብ ምዕራብ እና ጋምቤላ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች በአዲስ አበባ ማሠራጫ ዋጋ ባለ ሶስት ሊትር 314 ብር፤ ባለ አምስት ሊትር 510 ብር፤ ባለ 20 ሊትር በብር 2,003 ብር የትራንስፖርት ሂሳብ ታክሎ በኅብረት ሥራ ዮኒየኖች አማካይነት በማሠራጨት ገበያውን በማረጋጋት ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል።

ኮርፖሬሽኑ የተለያዩ ምርቶችን ገበያው በሚፈልገው መጠን በስፋትና በብዛት በማቅረብ ሙሉ ለሙሉ ገበያውን የማረጋጋት አቅም ላይ አልደረሰም የሚሉት አቶ አቻ፤ ለዚህም እጅግ ሰፊ የሆነ የመሠረተ ልማት፣ ትራንስፖርትና የካፒታል አቅም እንደሚጠይቅ ተናግረዋል። ይሁንና ወደፊት አቅሙን በማጠናከርና መሠረተ ልማቶችን በማሟላት ገበያን የማረጋጋት ሥራውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

ኮርፖሬሽኑ የአገር ውስጥ ምርትን ሰብስቦና አደራጅቶ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ ከማድረግ ባለፈ በሀገር ውስጥ እጥረት የሚታይባቸውን ምርቶች ከውጭ የሚያስገባ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አቻ፤ የኅብረተሰቡን ፍላጎት በአገር ውስጥ ምርት ለመሸፈን ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑንም ተናግረዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው ኮርፖሬሽኑ ባለፉት ሰባት ወራት ከዕቅዱ ከ70 በመቶ በላይ ማከናወን የቻለ ሲሆን፤ አጠቃላይ ለገበያ ባቀረባቸው ጤፍ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ጥራጥሬ፣ ስኳርና ሌሎች ምርቶች በሰባት ወራት 257 ሚሊዮን ብር ትርፍ ማግኘቱንም አስታውቀዋል። ትርፍ ሲባል እንደሌሎች ነጋዴዎች የተትረፈረፈ ትርፍ ማትረፍ እንዳልሆነም ጠቅሰው፣ ወጪውን በገቢ መሸፈን የሚያስችል መጠነኛ ትርፍ እንደሆነም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አቻ ገለጻ፤ ኮርፖሬሽኑ በተለይም አምራቹን ለማበረታታት በዋናነት ከፍተኛ ምርት ተመርቶ ገበያ በሌለባቸው አካባቢዎች በመግባት ምርቱን አውጥቶና አደራጅቶ እጥረት ወዳለበት ቦታ እንዲሸጥ በማድረግ ሰፊ ሥራ እየሠራ ይገኛል። በዚህም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚገበያዩባቸው ከ54 በላይ የአትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ ሱቆች አሉት። ፓስታ፣ማካሮኒና ሌሎች ምርቶች የሚሰራጩባቸው ደግሞ ከአራት በላይ ቦታዎች ሲኖሩት፣ ከ11 በሚበልጡ ቦታዎችም ስንዴ፣ በቆሎና ሲሚንቶ ያሰራጫል። ኮርፖሬሽኑ በአጠቃላይ 211 በሚደርሱ ማሰራጫና ማከፋፈያዎች የተለያዩ ምርቶችን በማቅረብ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች አገልግሎት በመስጠት ገበያ የማረጋጋት ሥራ እየሠራ ይገኛል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## እራትም ፣ መብራትም የለም

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

የእኛዎቹ አበው ሲተርቱ በምክንያትና በሰበብ ነው። ሁሌም እውነታን ይፈልጋሉ፣ ጥሬ ሀቁን ያስታክካሉ። ሲላቸው በተረትና ምሳሌው፣ ሲሻቸው በፈሊጥ ዕንቆቅልሹ የውስጣቸውን ያወጉናል፣ የልባችንን ያኩልናል። ታዲያ ያሉት ሁሉ ከመሬት ጠብ አይልም። ወይ ይኖሩታል ፣ አልያም አስቀድመው ያሳዩታል።

ክብር ለእነሱ ይሁንና ሰሞኑን ከአባባሎቻቸው መሀል አንዱን በአካል ቆሞ ባገኘው ከልቤ አደነቅኋቸው። ‹‹ራትና መብራት አታሳጣን›› ይባልን ምሳሌ። ወዳጆቼ ከሰሞኑ ራትም መብራትም ያጣ ሰው ይህን ምሳሌ ደጋግሞ ቢለው አይግረማችሁ። ለካንስ እውነታቸውን ኖሯል ራትን ከመብራት ማጋባታቸው ያሰኛል።

በቅርቡ ከመንደራችን እንደልማዱ መብራት ጠፋ። ይህን ስላችሁ መብራት መጥፋት ብርቅ ነው እንዴ? ትሉኝ ይሆናል። እውነት ነው በተለይ ለእንደኛ አይነቱ ልማደኛ ሰፈር መብራት ድርግም ብሎ መጥፋቱ ፈጽሞ ብርቅ አይደለም። ምንአልባትም ብርቅ የሚሆነው ለቀናት የዘለቀ ብርሃን የማግኘታችን እውነት ሊሆን ይችላል። ለቀናት የዘለቀው የሰሞኑ መብራት መጥፋት ግን ከወትሮው በላቀ ብዙ አሳይቶናል።

ሰበበኛው የኛ ሰፈር ከሰሞኑ ጥቂት ካፊያና ንፋስ ሸው ሲለው አረፈደ። ሸውታው በጊዜ ሳይቋጭ ቀርቶም እስከ ማምሻው ዘለቀ። እንዲህ በሆነ ጊዜ ነዋሪው ያለቅጥ ይሰጋል። አብዛኛው እንደ ባለሙያ አየሩን መተንበይ ይዳዳዋል። ወዶ አይደለም። ያገኘ ቢያገኘው እንጂ።

የተፈራው አልቀረም። ምሽቱ መቃረቢያ ላይ እንደስለት ልጅ ዓይን ዓይኑን ሲታይ የዋለው መብራት ‹‹ ድ.ር.ግ.ም›› አለ። በየቤቱ ብስጭቱ ፣ መነጫነጩ፣ ወጣ ገባው ቀጠለ። ይህ አይነቱ ስሜት ለእኛ ሰፈር ብርቅ ሆኖ አያውቅም። መብራት ሲጠፋ ሁሉም ጓዳ ጓድጓዳውን እያሰበ ይቆዝማል፣ ግራ ይጋባል።

መቼም ‹‹ወዳጆቼ!›› ስራ ውላችሁ ቤት ስትገቡና ጨለማ ሲጠብቃችሁ የሚኖረውን ስሜት አትጠይቁኝ። በተለይ እንደእኔ ኮንዶሚኒየም ለሚኖር ሰው አሳር ፈተናው ይበዛል። ለስሙ ‹‹የጋራ መኖሪያ›› በሚባልለት ሕይወት ኑሮው ይከብዳል ፣ ምርጫው ይጠባል። ወጣ ብሎ እሳት መጫር፣ ዝቅ ብሎ ጉልቻ መወዘት ፣ ቅጠል አንድዶ በምጣድ መጋገር ፣ በድስት መስራት ይሉት ጉዳይ አይታሰብም።

አንዳንዴ ከአሁን አሁን የጠፋው መብራት ይመለሳል በሚል ለሊቱን በተስፋ የሚያጋምሱ አይጠፉም። በተለይ ቤታቸው ገብተው እንደነገሩ ለሚያድሩ ላጤዎችም ይህ አጋጣሚ በእጅጉ ይከብዳል። ያለራት ተጠቅልለው ከማደር ውጭ ምርጫ የላቸውም።

ብዙ ጊዜ በአካባቢው መብራት በጊዜ ከጠፋ ቤታቸው ሳይገቡ በጨለማው ደጅ የሚያመሹ ህጻናት አይታጡም። በለስ ቀንቶ መብራቱ በድንገት ብልጭ ካለ ታዲያ የእነሱን ጩኸትና ደስታ አለማየት ነው። ተዓምር የመጣ ይመስል አካባቢው በሆታና በዝላይ ይሞቃል። ከቤት ያለው ባለተስፋም ደስታው በእኩል ይደምቃል።

በኮንዶሚኒየም መንደር አብዛኛው በሩን ዘግቶ የመኖር ልማድ አለው። በዚህ የአኗኗር ዘይቤ ታዲያ ከጎረቤት እንጀራ ቆርሶ ከአንዱ ቤት ወጥ ጨልፎ የራት ወግን ማድረስ ቀልድ ይሆናል። በተለይ በምሽት መብራት ሲጠፋ ይህ አይነቱ ዕድል የጠበበ ነው። እናም ምርጫ የለም። ከሰል ማቀጣጠል ፣ ለእራት የሚቀል ዳቦ ፍለጋ መባዘን አይቀሬ ይሆናል። እሱን እንተወውና በሰሞኑ መብራት መጥፋት ላይ እናውጋ።

በሰፈሩ አንድ ምሽት ዓይንዓይኑን ሲታይ የዋለው መብራት በድንገት ድርግም አለ። እውነታው እንዳልኳችሁ ነው። ነዋሪው የመብራት መጥፋትን እንደ ባህል ተዋርሶታል። በጣም የሚገርመው የጎረቤቶቻችን መብራቶች እንደልማዳቸው ቦግ ብለዋል።

እንዲህ መሆኑ አዲሳችን አይደለም። ከፊት ከኋላ፣ ከቀኝ ከግራ፣ ከመንገድ ወዲህና ወዲያ ያሉ ሰፈሮች የጨረቃ ማህበርተኞች መስለው መኖራቸውን አሳምረን እናውቃለን። ሁሌም በእነሱ ደማቅ ብርሃን ምራቃችንን እንደዋጥን፣ እንደተቁለጨለጭን ነው። የዛን ዕለት ጊዜው መሽቷልና ሁሉም እንደነገሩ ሆኖ ለሊቱን አነጋው።

በማግስቱ የመብራት ሃይልን ነጻ የስልክ መስመር 905ን የሚደውለው በረከተ። ምላሽም ተስፋም ሳይኖር የፈራነው ምሽት ደረሰ። ህጻናት እንደልማዳቸው ተኮልኩለው የመብራት አቀባበል ሊያደርጉ ተዘጋጅተዋል። አንዳች ተስፋ የለም። ሁሉም አኩርፏል ፣ ተከፍቷል። በድንገት ግን ሲጠበቅ የቆየው ብርሀን ‹‹ ..ፏ.. ብልጭ›› አለ። ሁኔታውን መገመት አያዳግትም። አካባቢው እልልታ ቀረሽ የሆነ ደስታና ምስጋና ወረሰው።

ልጆቹ ጮሁ፣ ዘለሉ፣ የብዙዎች ፊት ፈካ፣ ደመቀ። የእንጀራ ሊጥ ያቦኩ ፈጥነው አቢስታቸውን ጣሉ ፣ ለልጆች ዳቦ ቂጣ ያሰቡ ዱቄት ዘግነው ለጋገራው ተጣደፉ። ሞባይሎች፣ ፓወር ባንኮች፣ የመብራት ቀፎዎች፣ ሃይል ሊሞሉ ከሶኬት ጫፍ ተደረደሩ።

ቡና ሱስ ሲያዛጋቸው የዋሉ ፣ ስኒ ደርድረው፣ ዕጣን አጭሰው የልብ ሊያደርሱ ተጣደፉ ፣ እንጀራው ሊጋገር ምጣዱ ሰማ፣ ሊጡ ቀጥኖ ተቀዳ።

ናፍቆታችን አላለቀም ፣ ደስታችን ብዙ አልቆየም። ‹‹ጠላታችሁ ድርግም ይበል›› መብራቱ በመጣበት ፍጥነት ‹‹ደህና እደሩ›› ብሎን እብስ አለ። ዕንባ ቀረሽ ኀዘን ከበበን። ህጻናት ማልቀስ፣ እናቶች ማዘን ያዙ። ሁላችንም እፍር ፣ ኩምሽሽ አልን። ለእነ እንቶኔ የማይደርሰው የእርግማን መዓት ከየቤቱ ተዥጎደጎደ። ልፉ ያለን።

ቀና ብዬ የወዳጅ ሰፈሮችን ምሽት በዓይኖቼ ቃኘሁ። እንደልማዳቸው ፏ ድምቅ እንዳሉ ነው። ቅናት ቢጤ ውስጤን ሲጎነትለው ተሰማኝ። ‹‹ውይ! ታድለው›› ኡፍፍፍ..... ።

አሁን የአበው ተረት በዓእምሮዬ ይመላለስ ያዘ። ውስጤ ‹‹ራትና መብራት አታሳጣን›› ይሉትን ምሳሌ ደጋግሞ አቀበለኝ። ‹‹ድንቄም ራት፣ ድንቄም መብራት›› በልቤ ክፉኛ አሽሟጠጥኩ። ‹‹ጽድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ›› አሉ ራትም መብራትም በሌለበት ዓለም የተረቱ ትርጉም አልገባሽ አለኝ። ተቃጠልኩ። ለነገሩ እውነት ነው፣ ራትም መብራትም ማጣት ክፉኛ ይከብዳል።

አይነጋ የለም ጨለማው ገፏል። የእኛ ሰፈር መብራት አሁንም እንደወጣ ነው። አልተመለሰም። እንደዋዛ አራተኛ ቀን ተቆጥሯል። ችግሩ ብሷል። የዳቦ ቤቶች ወረፋ አስፓልት ተሻግሯል። እናቶች የሊጥ ባልዲ ይዘው እንክርት ገብተዋል። በእንጨት ያስጋግራሉ በተባሉ ግቢዎች ድብድቡ ፣ስድድቡ ቀጥሏል።

መብራት ሃይሎች አሁንም መልስ እየሰጡ አይደለም። ዝም ጭጭ እንዳሉ ነው። ከወዲያኛው መንደር ሕይወት በርቷል። መብራቱ እንደደመቀ ውሎ ያመሻል። የእኛው ሰፈር ዛሬ አምስተኛውን የጨለማ ቀን እየቆጠረ ነው›። ነዋሪው በሰው አገር መብራት እየተደመመ ፣ በጎረቤት የምግብ ሽታ ራቱን ጠግቦ ማደር ይዟል።

ትናንትና ጠዋት መብራት ሃይል መግለጫ ሰጠ አሉ። ‹‹በከተማው የተከሰተው የመብራት መጥፋት ችግር በመስመሮች ላይ የደረሰ ብልሽት ነው›› ሲል። እኔ የምለው በተለይ የእኛው የጀሞ አንድ አካባቢ ችግር ከሌሎች ይለያል እንዴ? ትራንስፎርመሩ በስንደዶ የተሰራ ይመስል በየቀኑ ተቃጠለ ፣ ነደደ እንባላለን። መስመሮቹ ስሪታቸው ከዳንቴል ክር ይመስል በየጊዜው ተበጣጥሰው መውደቃቸው ይሰማል።

ቡራቡሬው የመንደራችን ገጽታ በብርሃንና ጨለማ ተዥጎርጉሮ፣ በመብላት አለመብላት ተለያይቶ ቀናትን ዘልቋል። ቡሄ ቢደርስ ኖሮ የእኛ ሰፈር ራት አልባ ህጻናት ሆያ ሆዬውን እንዲህ ይሉት ይመስለኛል።

እዛ ማዶ ! ሆ ! አንድ እራት
እዚህ ማዶ! ሆ! አንድ እራት
የእኔማ እንቶኔ ባለመብራት።
ወዳጆቼ! እራትም መብራትም ከማጣት ያውጣችሁ።

# ዓለም አቀፍ



## አደጋ በደረሰባት ጀልባ ላይ የነበሩ 30 ስደተኞች ሜዲትራኒያን ላይ የደረሱበት ጠፋ

ከሰሜን አፍሪካዊቷ ሊቢያ የባሕር ዳርቻ ስደተኞችን የጫነች ጀልባ በሜዲትራኒያን ባሕር ላይ ተገልብጣ 30 ሰዎች የደረሱበት ጠፍቷል።

ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ወደ አውሮፓ ለመሻገር የተነሱ ስደተኞችን ያሳፈረችው ጀልባ አደጋው ከደረሰባት በኋላ 30 የሚደርሱት ሰዎች ሳይሞቱ እንዳልቀረ ተሰግቷል።

በባሕር ላይ አደጋ የሚገጥማቸውን ስደተኞች የሚታደገው ‘አላርም ፎን’ የተባለው የሰብአዊ እርዳታ ቡድን፣ የአውሮፓ አገራት ለስደተኞቹ የግድየለሽነት አቋም ባይዙ ኖሮ ደብዛቸው የጠፋውን ሰዎች ማዳን ይቻል ነበር ብሏል።

የበጎ አድራጎት ቡድኑ እንዳለው በጀልባዋ ላይ ከነበሩት ስደተኞች የድረሱልን ጥሪ ከደረሰው በኋላ የሊቢያን፣ የጣሊያንን እና የማልታን ባለሥልጣናት ስለአደጋው የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ነበር።

የጣሊያን የባሕር ጠረፍ ጠባቂዎች ግን፣ ጀልባዋ በሊቢያ ጥበቃ በሚደረግበት የባሕሩ ክፍል ውስጥ የነበረች በመሆኑ እንዲሁም በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ወደ ቦታው መድረስ አዳጋች እንደበር ገልጿል።

የሊቢያ ባለሥልጣናት በበኩላቸው የነፍስ ማዳን ተግባር ለማከናወን የሚያስችላቸው ጀልባዎች እንዳልነበሯቸው ገልጸዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## ባይደን ከሰጡት ማረጋገጫ በተቃራኒ የአሜሪካ ባንኮች የአክሲዮን ድርሻ አሽቆለቆለ

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን የአሜሪካ የፋይናንስ ሥርዓት አይንገራገጭም የሚል ቃል ቢሰጡም ከትናንት በስቲያ መጋቢት 4/2015 ዓ.ም ሆኖ የታየው ግን በተቃራኒው ነው። በዕለቱ በዓለም ዙሪያ የባንኮች የአክሲዮን ድርሻ ዝቅ ብሏል።

ለቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ብድር በማቅረብ የሚታወቀው ሲልከን ቫሊ ባንክ እንዲሁም ሲግኒቸር ባንክ ኪሳራ ያጋጠማቸው ሲሆን የደንበኞችን ተቀማጭ ገንዘብ ለመጠበቅ የአሜሪካ መንግሥት እርምጃ ወስዷል።

ጆ ባይደን የባንክ ሥርዓቱን ለመጠበቅ “የሚያስፈልገው ሁሉ” ይደረጋል ሲሉ ቃል ገብተው ነበር። ሆኖም በዓለም አቀፍ ደረጃ ባጋጠመው የአክሲዮን ድርሻ ማሽቆልቆል ምክንያት የባንክ ባለድርሻዎች ሌሎችም ባንኮች ሊጎዱ ይችላል የሚል ስጋት አድሮባቸዋል።

ትናንት የስፔኑ ስታንዳርድ ባንክ እንዲሁም የጀርመኑ ኮሜርዝ ባንክ የአክሲዮን ድርሻቸው እስከ 10 በመቶ ዝቅ ብሎ ተመልክተዋል።

በርካታ የአሜሪካ አነስተኛ ባንኮች ደንበኞቻቸውን ከችግር የሚታደጉበት ወደ ገንዘብ ሊቀየር የሚችል ከበቂ በላይ ሀብት እንዳላቸው ቢገልጹም፤ ከአውሮፓውያኑ መሰል ተቋማት በከፋ ሁኔታ ኪሳራ አጋጥሟቸዋል።

ይህ ባንኮች ላይ ያጋጠመው ችግር የአሜሪካ ባንክ የአሜሪካ ግምጃ ቤት የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር የወለድ ምጣኔ ላይ የሚያደርገውን ጭማሪ እንዲገታ ሊያደርገው ይችላል የሚል ግምቶች እንዲበራከቱ አድርጓል።

መንግሥት የተቀማጭ ገንዘብን ለመጠበቅ እርምጃ ከወሰደ በኋላ ፕሬዚዳንት ባይደን ሲልከን ቫሊ ባንክ ውስጥ ተቀማጭ ገንዘብ ያላቸው ግለሰቦችም ይሁኑ የንግድ ተቋማት ከሰኞ ጀምሮ ማንቀሳቀስ ይችላሉ ብለዋል።

በርካታ የንግድ ተቋማት ባጋጠመው ችግር ገንዘባቸው መታገዱን ተከትሎ ለሰራተኞቻቸው እና አቅራቢዎች ገንዝብ መክፈል እስካለመቻል ደርሰው ነበር።

ቢቢሲ በሲልከን ቫሊ ባንክ ገንዘባቸውን ለማውጣት በካሊፎርኒያ የተሰለፉ ደንበኞችን ተመልክቷል። ባንኩ በኢንተርኔት ገንዘብ የሚወጣበትን ሥርዓት ማቆሙን ተከትሎ ደንበኞች ገንዘባቸውን በጥሬ ለማውጣት ተገደዋል።

ለቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ብድር በማቅረብ የሚታወቀው ሲልከን ቫሊ ባንክ በአሜሪካ መንግሥት ተዘግቷል። ባለፈው አርብ ደግሞ ንብረቱ ተይዞ ነበር። ለአሜሪካው ባንክ ይህ እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን ስሌት በ2008 ካጋጠመው የፋይናንስ ቀውስ በኃላ የተከሰተ ትልቁ ኪሳራ ነው።

ባንኩ ንብረቶቹን በመሸጥ በከፍተኛ ወለድ ምክንያት ያጋጠመውን ኪሳራ ለመቋቋም ሲሞክርም ነበር። ያጋጠመው ችግር ደንበኞች ገንዘባቸውን ለማውጣት እንዲጣደፉ ምክንያት ሆኗል። ይህም ባንኩን ለገንዘብ ቀውስ ዳርጎታል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

**ማህበራዊ**

# ባለውለታዎቻችን

# "የሥነ-ጽሁፍ ዋርካ"

## ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ሲታወሱ

**ማህሌት አብዱል**



ኢትዮጵያ ባሳለፍነው ሳምንት መጀመሪያ ላይ ታላቁን የሥነ-ጽሁፍ ሰው ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋውን አጥታለች።ይህ ድንገተኛ የሞት ዜና በእሳቸው እጅ ተምረውና ተኮትክተው ካደጉ፤ ትልቅ ደረጃ ከደረሱ ተማሪዎቻቸው ጀምሮ መላውን የኪነ-ጥበብ ማህበረሰብ ልብ የነካ ሆኖ አልፏል። በተለይም ደግሞ እኚህ ሥራ ወዳድ የሥነ-ጽሁፍ ሰው ባለፈው ሳምንት ሰኞ ለሊት ድረስ በቤታቸው በሥራ ላይ የነበሩ እና ከዚያ በፊት ባሉት ቀናትም ፍፁም ጤነኛ ሆነው መክረማቸውን የሚያውቅ ቤተሰብ፤ የቅርብ ጓደኛና አድናቂያቸው በድንገት ታመው ለሕልፈት የመዳረጋቸውን ጉዳይ ዛሬ ድረስ አምኖ ለመቀበል መቸገሩን በመገለጽ ላይ ይገኛል።

የአንጋፋው መምህር ሥርዓተ ቀብር የመንግሥት የስራ ሃላፊዎች ፣ ምሁራን ፣ ወዳጅ ዘመዶቻቸው ፣ የስራ ባልደረቦቻቸው ፣ የሥነ-ፁሑፍ ባለሙያዎች፣ ደራሲያን ፣ ጋዜጠኞች እንዲሁም አድናቂዎቻቸው በተገኙበት ረቡዕ የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም በቅድስት ስላሴ ካቴድራል ቤተክርስቲያን በታላቅ ክብር ተፈጽሟል። በሥርዓተ ቀብራቸው ላይም የተገኙ ታላላቅ ሰዎች ጋሽ ዘሪሁን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በመምህርነት ባገለገሉባቸው አራት አስርት ዓመታት ሁሉ "ማስተማርን ፈጣሪ በተለየ መንገድ እንደሰጣቸው ፀጋ ተቀብለው ትውልድን ለማነፅ ዋጋ የከፈሉ የትምህርት አባት እንደነበሩ የመሰከሩላቸው ሲሆን ‹‹የሥነ ጽሁፍ ዋርካው ወደቀ›› በማለትም ኀዘናቸውን ገልጸዋል፡፡

በማስተማር ሥራቸው ብቻ ሳይሆን በጥናት እና ምርምር ሥራዎች ላይ ባስቀመጡት የጊዜ ገደብ ማከናወንን የሚመርጡ ፤ ሰዓት አክባሪና ሰው ለመርዳት ቀዳሚ የሆኑ ሰው እንደነበሩ የሚነገርላቸው ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ጥቅምት 10 ቀን 1944 ዓ.ም በደሴ ከተማ መወለዳቸውን የታሪክ ማህደራቸው ያስረዳል። የመጀመሪያ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በደሴ አካለወልድ ትምህርት ቤት እና በወይዘሮ ስህን ትምህርት ቤት ተከታትለዋል።በተለይም በወይዘሮ ስህን ትምህርት ቤት በነበራቸው ቆይታ ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የትምህርት ቤቱ የኪነ-ጥበብ አባል በመሆን በቲያትር ትወና ፣ በሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋችነት የሚሳተፉ ንቁ ተማሪ እንደነበሩ ይጠቀሳል።ይህም ታዲያ በኃለኛው ዘመን እድሜያቸውን ሙሉ ለቆዩበት የሥነ-ጹሑፍ ሕይወታቸው መሰረት ጥሎላቸዋል።

ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን በ1962 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በልዑል በዕደ-ማርያም የመሰናዶ ትምህርት ቤት መማር ከጀመሩ በኋላ የጥበብ ጥሪውን በመከተል የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ የባህል ማዕከል አባል በመሆን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ የነበራቸውን ኪነ-ጥበባዊ ጥሪያቸውን ገፍተውበታል።በመቀጠልም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎችና ሥነ-ጹሑፍ ትምህርት ክፍል ከ1963 ዓ.ም ገብተው መማር ጀመሩ።በወቅቱ አስፈላጊ በነበረው የዩኒቨርሲቲ አገልግሎት በመሳተፍ በኤርትራ ጠቅላይ ግዛት በከረን ከተማ ለአንድ አመት ያህል አስተምረው ግዳጃቸውን ተውጥተው ተመልሰዋል።እንዲሁም ደግሞ በ1967 ዓ.ም በታወጀው የእድገት በህብረት የዕውቀትና የስራ ዘመቻ ተሳታፊ በመሆን በትግራይ ጠቅላይ ግዛት በዓድዋና አካባቢው ተመድበው የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት መቻላቸው ይነገራል።

በዩኒቨርሲቲ አገልግሎትና በእድገት በህብረት ዘመቻ ምክንያት ለሶስት ዓመታት ያቋረጡትን ትምህርት ለመቀጠል ቢሞክርም በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ኃይሎች ትርምስ በቀይና ነጭ ሽብር ምክንያት ተረጋግቶ መማር ባለመቻላቸው በቀድሞው አጠራር አሩሲ ክፍለ ሀገር አሰላ ከተማ በመሄድ አሰላ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማርኛና እንግሊዝኛ ትምህርት ለአንድ ዓመት አስተማሩ።ከዚያም ተመልሰው ያቋረጡትን ትምህርት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል በ1970 ዓ.ም የመጀምሪያ ዲግሪያቸውን አገኙ።የሁለተኛ ዲግሪያቸውንም ከዚሁ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውጭ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ተቀብለዋል፡፡

ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪውን ካገኙ በኋላ በዩኒቨርሲቲው ስር በነበረው የዓለማያ ግብርና ኮሌጅ በረዳት ምሩቅነት ደረጃ በ1971 ዓ.ም የተቀጠሩ ሲሆን እስከ ዩኒቨርሲቲ መምህርነት ደረጃ ደርሰዋል። በመቀጠልም 1975 ዓ.ም በመምህርነትና በተከታታይ ትምህርት አስተባባሪነት ሰርተዋል። ከ1976 ዓ.ም ጀምሮ ህይወታቸው እስካለፈበት ድረስ በአዲስ አበባ ዩሚቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋና ፎክሎር ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ውስጥ በተለያዩ ማዕረጎችና ኃላፊነቶች ላይ አገልግለዋል።

ላለፉት 40 ዓመታት ከመጀመሪያ ዲግሪ ጀምሮ እስከ ዶክትሬት ዲግሪ ድረስ በርካታ ተማሪዎችን በማፍራት የሚታወቁት ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከማስተማር ጎን ለጎን 143 የመጀመሪያ ዲግሪ 80 የማስተርስ ዲግሪ 20 የዶክቶሬት ዲግሪ ተማሪዎችን በምርምር ስራዎቻቸው ማመከራቸውን ከግለ- ታሪካቸው ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። ከዚህም ባሻገር በተለያዩ ሥነ ጽሑፋዊ ጉዳዮች ላይ ጥናትና እና ምርምሮችን ያካሄዱት ተባባሪ ፕሮፌሰሩ፤ ከትምህርቱ ዘርፍ በተጨማሪ ከፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር ጋር በመሆን የተለያዩ የሥነ ሕዝብ ጥናቶችን ሰርተዋል። እንዲሁም ወጣት ደራሲያን እና ተመራማሪዎችን በማማከር እና በመደገፍ ትልቅ አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡

በጥናት እና ምርምር ሥራዎች ላይ "የኢትዮጵያን ሥነጽሑፍ ታላላቅ የሥነጽሑፍ ስራዎችን የሰነዱ" ታላቅ መምህር የነበሩት ጋሽ ዘሪሁን ከምርምር ስራዎቻቸው በተጨማሪ እነዚህም የሥነ-ጽሁፍ መሠረታውያን ልቦለዳውያን እና የቀደምት ደራስያን አጫጭር ትረካዎች ፣ ሥነ-ጽሑፍ ለማህበራዊ ለውጥ ፣ ከበዓሉ ግርማ እስከ አዳም ረታ እንዲሁም በሥነ-ጽሑፍና በፎክሎር የተሰሩ የዲግሪ ማሟያ ጥናቶችና አጠቃሎ ስብስብ የሚሉ አምስት መጽሐፍትን አሳትመው ለንባብ አብቅተዋል፡፡

በተጨማሪም ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የምርምር እና የጥናት ስራዎችን በታወቁ የጥናት መጽሔቶች እና ታላላቅ ጉባዔዎች ላይ የታተሙላቸው ሲሆን አሁንም ድረስ በርካታ ያልታተሙ ስራዎች ያሏቸው መሆኑን ከቅርብ ጓደኞቻቸው ለማወቅ ተችሏል።ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው በሀገር ውስጥ ካበረከቷቸው ተሳትፎ በተጨማሪ በዓለም አቀፍ መድረኮችም ተሳታፊ ነበረ።ከእነዚህ መካከልም በአሜሪካ ፣ በጃፓን ፣ ደቡብ አፍሪካ ፣ ዛምቢያ ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ እንግሊዝ እና ጀርመን የሚገኙ ቀዳሚ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በትምህርት ቤት የኪነ-ጥበብ ክበብ የጀመረውን የተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ንቁ ተሳታፊነት ቀስ በቀስ እያሳደገና እያጠናከረ ሕይወታቸውን ድርና ማግ ያደረገ በጥልቅ ተመልካችነት ሥነ-ጽሁፍን የተጠበበ፤ የመረመረ የሄሰ፤ የሀገሪቱን አንጋፋና ወጣት ተመራማሪዎችንም ሆነ ፈጣሪዎች በረቂቁ የአስተሳሰብ መንገድና የአሰራር ብልሃታቸው ያስገኙትን ትሩፋት አንጥሮ በማሳየት ዘወትር የሚተጉ ነበሩ።

ከመጀመሪያ ዲግሪ ጀምሮ እንዳስተማሩት ለቢቢሲ የተናገረው ዶክተር አንዱዓለም አባተ በበኩሉ፤ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን "በአስተማሪነቱ ለራሱ፣ ለትምህርት ክፍሉ፣ በትምህርት ክፍሉ ውስጥ ላሉ እና ተማሪው ለሆኑ ሁሉ አርዓያ የሆነ" ሲል ይገልጿቸዋል። ‹‹የኢትዮጵያን ሥነጽሑፍ የሰነዱ›› መሆናቸውን አመልክቶ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስገራሚ የማስታወስ ችሎታ እንደነበራቸውም ያስረዳል። ‹‹በማስተርስ እና በፒኤችዲ ያስተማራቸውን ተማሪዎች ሳይቀር በምን ጉዳይ ጥናታቸውን እንደሰሩ፣ ምን ክፍተት እንደነበረባቸው እና ጥናታቸው፣ ምን ጠንካራ ጎን እንደነበረው ሰንደው የያዙ ነበሩ›› ይላል።

አንዱዓለም ብዙ ጊዜ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ የጥናት ርዕስ መደራረብ እንደሚያጋጥም፣ በአንዱ ዩኒቨርሲቲ የተጠናውን ደብቀው አምጥተው ሌላ ዩኒቨርሲቲ የሚያጠኑ መኖራቸውን አስታውሶ "ማን ምን አጠና የሚለው ዝርዝር መረጃ በእኛ የትምህርት ክፍል ያለው እርሱ ጋር ነው" በማለትም ያክላሉ። እኒህን ሰው ማጣት «የተደገፍክበት ወንበር ድንገት ሸርተት ሲልብህ» ያለውን ስሜት የሚፈጥር ነው በማለትም ነው ከያኒ አንዷለም አባተ ለቢቢሲ ዘጋቢ በሞታቸው የተሰማውን ኀዘን የገለጸው።

ከ1976 ዓ.ም ጀምሮ እንደሚያውቋቸው ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን በሥራቸው የተመሰገኑ እንደነበሩ ሌላው ለቢቢሲ የተናገሩት ደግሞ ረዳት ፕሮፌሰር ደረጀ ገብሬ ናቸው።ተባባሪ ፕሮፌሰሩ ለዘርፉ እድገት ካበረከቷቸው በርካታ ስራዎች በተጨማሪ የሌሎች ሰዎች ሥራዎችን አርትኦት በማድረግም ከፍተኛ ሚና መጫወታቸውን ነው የጠቆሙት። ከዚህም ባሻገር ለህትመት ዝግጁ የሆኑ "ሁለት ወይም ሦስት ሥራዎች" እንዳሏቸውም አመልክተዋል።

ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ካስተማሯቸው ብዙ ደራሲያን መካከል በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ሥራ አስኪያጅ ሆነው የሚያገለግሉት እና በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ ሴት የአጭር ልብ ወለድ አሳታሚ ወይም ጸሐፊት የዝና ወርቁ አንዷ ናቸው።

«ጋሽ ዘሪሁን ትዕግስተኛ ፣ መካሪ ነበር። ኢትዮጵያ እጅግ ታላቅ የሥነ ጽሑፍ ምሁር ነው ያጣችው» ብለዋል።

‹‹ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው የሚለውን ሥም ከብዙ ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ ሬዲዮ ቅዳሜ የኪነ- ጥበባት ምሽት በተባለው ዝግጅት ላይ በኢትዮጵያ ስለ የመጀመርያው አጭር ልብ ወለድ 'የጉለሌው ሰካራም' ጥናት ሲያቀርብ ነበር የሰማሁት›› በማለት የተናገረው ደግሞ ደራሲ እንዳለ ጌታ ከበደ ነው። ከዚያ በኋላ ይበልጥ መተዋወቃቸውንና ቅርበታቸውን መጠናከሩን ነው በኀዘን ስሜት የገለጸው።

ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው በኢትዮጵያ የሥነ- ጽሑፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደነበራቸው ጠቅሶ፤ ከዚህም በላይ በዘርፉ ብዙ የሕይወት ልምዶች እንደነበሯቸው ፣ ነገር ግን «ምን ሠራሁ» የሚል ትህትና የተላበሱ እና በመገናኛ ብዙኃን ብዙም ቀርበው የማይታዩ የማይደመጡ ቁጥብ ሰው እንደነበሩ አስታውሷል።

አድናቂዎቻቸው ‹‹የሥነ-ጽሁፉ ዋርካ›› እያሉ የሚያቆላምጧቸው ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው በተወለዱ በ71 ዓመታቸው የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም በድንገት ባደረባቸው ህመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ለ40 ዓመታት በትዳር አብረው ከቆዩዋቸው ባለቤታቸው ከወይዘሮ የትምወርቅ አካሉ አምስት ልጆች አፍርተው እንደነበር የሕይወት ታሪካቸው ያሳያል።

በተለያዩ ሥነ ጽሑፋዊ ጉዳዮች ላይ ጥናት እና ምርምሮችን በመስራት እንዲሁም በሃያሲነታቸውም ይታወቃሉ።

# ስፖርት





## በውሹ ስፖርት ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ዓለም አቀፍ ሥልጠና ሊሰጥ ነው

**አስማየሁ ግዛው**

በኢትዮጵያ ውሹ ስፖርት ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የአሠልጣኞች ሥልጠና እንደሚሰጥ ተገለጸ። የሥልጠናው አዘጋጅ የኢትዮጵያ ውሹ ፌዴሬሽን ሲሆን በአሁኑ ወቅት የፈረንሳይ ብሔራዊ ቡድን የውሹ ስፖርት አሠልጣኝ የሆነው ቻይናዊው ማስተር ሑ ሊን ሥልጠናውን እንደሚሰጥ ተጠቁሟል።

ሥልጠናው ከመጋቢት 8 እስከ መጋቢት 10 /2015 ድረስ ለሶስት ቀናት በኢትዮጵያ ወጣቶች አካዳሚ ይሰጣል። በሥልጠናው ጀማሪ አሠልጣኞች፣ መካከለኛ ኢንስትራክተሮች፣ ከፍተኛ ሲኒየር ማስተሮች የሚሳተፉ ሲሆን ሥልጠናውን የሚያጠናቅቁ ሠልጣኞች ከውጭ የሚመጣ ዓለም አቀፍ የምስክር ወረቀት እንደሚበረከትላቸው ታውቋል።

ይህ ሥልጠና ከዚህ በፊት በፌዴሬሽኑ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እና በክልል ፌዴሬሽኖች በኩል ለረጅም ጊዜያት ሲጠየቅ የነበረ እና ለስፖርቱ እድገትም ሆነ ለባለሙያው እጅግ አስፈላጊ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች እና በሁኔታዎች አለመመቸት ምክንያት ከዚህ በፊት ማዘጋጀት ሳይቻል ቆይቷል፡፡

ሥልጠናው በፌዴሬሽኑ እና በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ከፍተኛ ዝግጅት የተደረገበት እና ለቀጣይ ዓለም አቀፍ ሥልጠናዎችም በር ከፋች እንደሚሆን ተታምኖበታል፡፡ በመሆኑም ሥልጠናው ግቡን እንዲመታ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ የስፖርቱ አሠልጣኞችን ተሳትፎ ይጠይቃል ተብሏል፡፡

የሥልጠናው ስፖርቱን በበሰሉና እውቀቱ ባላቸው ባለሙያዎች ለመምራት የሚደረግ ጥረት መሆኑም ተገልጿል፡፡ በሥልጠናው ከሁሉም ክልልና ከተማ መስተዳድሮች ጥሪ የተደረገላቸውና መስፈርቱን የሚያሟሉ አሠልጣኞች ተሳታፊ እንደሚሆኑ ተነግሯል፡፡ በሥልጠናው የሚሳተፉ አሠልጣኞች ከጥቁር ቀበቶ ጀምሮ እስከ ስድስተኛ ዳን ያላቸዉ እንደሆነም ታውቋል፡፡ ቁጥራቸው ከ200 እስከ 250 የሚደርሱ አሠልጣኞች ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የኢትዮጵያ ውሹ ፌዴሬሽን የውድድርና ሥልጠና ባለሙያ አቶ ገበየው ሙሉጌታ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፣ ስፖርቱ በባህሪታ የፍልሚያ ስፖርት ሲሆን፣ በኢትዮጵያ በተደረገ ጥናት ከፍልሚያ ጥበብ ጋር ተያይዞ ሰፊ ክፍተቶች አሉበት። በዚህም መሰረት ያለውን ክፍተት ለመሙላት ሥልጠናውን ለመስጠት ፌዴሬሽኑ መወሰኑን ባለሙያው ጠቁመዋል፡፡ ሥልጠናው ከዚህ ቀደም ከሚሰጡት ሥልጠናዎች ለየት የሚያደርገው ዓለም አቀፍ ደረጃዉን የጠበቀና ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሰጥ መሆኑ ነው። እንደ አቶ ገበየው ገለፃ፣ በከዚህ ቀደም አሠልጣኞች ወደ ቻይና ተልከው ለስድስት ወርና ለአንድ ዓመት ሥልጠናዎችን ይወስዱ ነበር። በዚህም ወደ ሰላሳ ስምንት የሚደርሱና ከተለያየ ክልልና ከተማ አስተዳደር የተውጣጡ ባለሙያዎችን ማሠልጠን ተችሏል። በተንጠባጠበ ሁኔታ ውጭ ልኮ ሥልጠና በመስጠት ውጤታማ መሆን ስለማይቻል ግን አንዴ ባለሙያ በማምጣት በርካታ አሠልጣኞችን ለማሠልጠን ተወስኗል።

ከሥልጠናው በኋላ በሚደረጉት አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ውድድሮች በሳንሹ (በፋይት) የተሻሉና ሀገርን የሚወክሉ ስፖርተኞችን ለመምረጥ ጥሩ አጋጣሚ መፍጠር እንደሚቻልም ባለሙያው አስረድተዋል። ለዚህም እንዲሆን ከወራት በኋላ የኢትዮጵያ ውሹ ቻምፒዮና እንደሚዘጋጅ ታውቋል። ሥልጠናውን የሚወስዱት አሠልጣኞች ለውድድሩ ይዘው በሚቀርቡት ተወዳዳሪ ላይ የሚታይ የቴክኒክ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻልም ባለሙያው ተናግረዋል።

ሥልጠናውን ከዚህ ቀደም በሀገር ውስጥ መስጠት ያልተቻለበት በርካታ ጉዳዮች መኖራቸውን የጠቆሙት ባለሙያው፣ ለስፖርቱ ትኩረት አለመሰጠት አንዱ ችግር መሆኑን አስረድተዋል። ከመንግሥት ጀምሮ ሚዲያና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለስፖርቱ ትኩረት መስጠት ከቻሉ ግን በቀላሉ ውጤት ማምጣት ከሚቻልባቸው የስፖርት አይነቶች ውሹ አንዱ እንደሚሆን ተናግረዋል።

"የውሹ ስፖርት ብዙ ማህበረሰብን በማቀፍ በትንሽ ወጪ ውጤት ማምጣት የሚቻልበት ነው" ያሉት አቶ ገበየው ስፖርቱ በሁሉም ክልሎች የሚዘወተር ስፖርት መሆኑን ተናግረዋል። ኦሮሚያ ክልል ብቻ በ2012 ላይ በተሰራው ዳታ ከ4ሺ 800 በላይ የውሹ ማሠልጠኛ ማዕከላት ያሉ ሲሆን በአዲስ አበባም በተለያየ ዲቪዚዮን በዓመት ሁለት ጊዜ የሚደረግ ውድድር አለ።

ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በውሹ ስፖርት በአፍሪካ ቻምፒዮናና በጥቂት ዓለም አቀፍ ውድድሮች ተሳታፊ መሆን ችላ እንደነበር ያስታወሱት ባለሙያው፣ በቀጣይም በአህጉርና ዓለምአቀፍ ወድድሮች ተሳትፎ ለማድረግ ጥረት እንደሚደረግ ተናግረዋል። ስፖርቱ በ2026 የኦሊምፒክ ስፖርት እንደሚሆን ቃል በመገባቱ ስፖርቱ በዓለም ላይ ምን ያህል ተወዳጅነትን እያተረፈ እንደመጣ ያሳያልም ብለዋል፡፡ በዚህም ፌዴሬሽኑ ሥልጠናዎችን ከመስጠት ባሻገር ተተኪዎችን ለማፍራት የተለያዩ ስራዎችን ከወዲሁ በመስራት ላይ ይገኛል። በአራት ክልሎች የታዳጊ ፕሮጀክቶች ተከፍተው በትግራይ፣ ደቡብና አማራ ክልል እየተሰራባቸው ነው። ይሁን እንጂ በሚፈለገው ደረጃ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ የፋይናንስ እጥረት የፌዴሬሽኑ ችግር ሆኗል። ስፖርቱን በተመለከተ ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆኑም በቀጣይ የማስተዋወቅ ስራዎች በስፋት እንደሚሰሩ ባለሙያው አክለዋል።


## አዲስ አበባ አስተዳደር

በይግባኝ ባይ አቶ ሚኒሊክ መዓዛ በመልስ ሰጪ እነ አቶ ሽመልስ ንጉሴ መካከል ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ 2ኛ መልስ ሰጪ አቶ አቤኔዘር በየነ 3ኛ መልስ ሰጪ አቶ አቡሽ አግዘው ለመጋቢት 25 ቀን 2015 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጧዋቱ 3፡30 ሰዓት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት 1ኛ ፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ሄኖክ መሳፍንት አለባቸው የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A37483 የተሽከርካሪው አይነት የመስክ ተሽከርካሪ የሻሲ ቁጥር JMYLNV76W4J001257 ሞዴል V76WLNHFL የሞተር ቁጥር 4M40GK7044 የሊብሬ ቁጥር 442259 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 28/6/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አገኘው ሲሳይ ደመላሽ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-70473 የተሽከርካሪው አይነት አውቶቡስ (ከ11 የበለጠ መቀመጫ) የሻሲ ቁጥር LL3AHADKOFA000414 ሞዴል XML6117J12Q የሞተር ቁጥር L300-20*78068447* የሊብሬ ቁጥር 0256184/0294516 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 1/7/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ኮኔል ኃላ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-85044 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻሲ ቁጥር LLV2A2A17C0063173 ሞዴል LF7130A4 የሞተር ቁጥር LF479Q3*120401419* የሊብሬ ቁጥር 236132 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 28/6/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ልደታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አመልካች አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም በተጠሪ የሺእመቤት ክፍለ ማርያም መካከል ስላለው ፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 1ኛ ፍ/ር ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ አውቀው መልስዎን በጽሁፍ ለ15/07/2015 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት ይዘው እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ ወ/ሮ ዝናሽ ክፍሉ መስፍን በተከሣሽ አቶ ደበበ መስፍን መካከል ስላለው የቤተሰብ ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ የሰጠው ትዕዛዝ ተከሣሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቂርቆስ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ የጋዜጣ ማስታወቂያ አውቀው መልስዎን በጽሑፍ ለ22/07/2015 ዓ.ም. በ3፡30 ሰዓት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት**

የባለንብረት ስም ውዴ መሹ ቡልቶ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01 A30342 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር JAMKP34G747P04538 ሞዴል NPC65K የሞተር ቁጥር 4HF1-062359 የሊብሬ ቁጥር 446496/450440 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 29/6/2015 አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም መስፍን ሐይሌ አያኖ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B46771 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር NMTKY3BX10R031072 ሞዴል NGX50L-AHXGXW የሞተር ቁጥር 8NR U130328 የሊብሬ ቁጥር 472185 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 29/6/2015 አመልክተዋል፡፡ የለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ልደታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**